


ቅዱስ ያሬድ ከእነ መማሪያው

# ትንሣኤ



የየካ ደብረ ሣህል ቅ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፩፻፵፪

የግንቦትና የሰኔ ፲፱፻፹፪ ዓ/ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ፡፡»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና
ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ፡፡

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

## ማውጫ

## ርእስት

ገጽ

ደብዳቤዎች ........................ ፩
(ርእስ አንቀጽ (ከአካል ክፍሎች አንዱ ቢታመም
ሁሉም ይሠቃያሉ ........................ ፪
ቅዱስነታቸው ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ ........................ ፬
ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ........................ ፭
የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........................ ፯
ዝናብን የምትጠጣ ምድር ........................ ፱
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........................ ፲
እልክላችኋለሁ ........................ ፲፩
የየጭቃ ማርያም ቤ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ ........................ ፲፫
ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ........................ ፲፭
የሴቶች ዓምድ ........................ ፲፮
ዜና ዕረፍት ........................ ፲፯
ወርኃ ክረምት ........................ ፲፱
አምልኮት ........................ ፳፩
ትምህርት ለሁሉም ይዳረስ ........................ ፳፪
ጤናችን ........................ ፳፫
ጋብቻና ኅብረተ ሰብእ ........................ ፳፬

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት
አዘጋጅ
አዲስ አበባ
ከሁሉ አስቀድሜ እኛን ከነጤ አት ቀምበር ነፃ ባወጣን በጌታችን በመድኃኒታችንና በአምላካችን ኢየሱስ ስም ሰላምታዬን አቀርባለሁ ፡፡

ስለቤተ ክርስቲያን ባሕል ወግና ሥነ ሥርዓት የሚያከናውን የትንሣኤ መጽሔትን በመከታተል በርከት ያሉ ቁምነገሮችን አግኝቸበታለሁ ፡፡

በመሆኑም የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ፡ ፩ኛ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጸሎት ምን ትላለች በጸሎት ጊዜ ዓይን እንዲጨፈን ታዛለችን?

፪ኛ/ ካህናት የሚይዙት የእጅ መስቀል ፬ ማዕዝን ልዩ ልዩ ቅርጻ ቅርጽ የሚደረግበት የምን ምሳሌ መሆኑን እንዲገለጽልኝ ፡

፫ኛ/ የቅዱስ ጳውሎስ የትውልድ ሀገሩ የት ነው?

፬ኛ/ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን የእምነት ልዩነታቸው እንዴት ነው?

፭ኛ/ ሰቆቃወ ኤርምያስን የጻፈ ማን ነው?

፮ኛ/ በጾም ወቅት የሚበሉና የማይበሉ የትኞቹ ናቸው? ዓሣ ከየትኛው ክፍል ነው?

፯ኛ/ ሥርዓተ ተክሊል ከተፈጸመ በኋላ ምን መደረግ አለበት?

፰ኛ/ የትንሣኤ መጽሔት በወር አንድ ጊዜ እየታተመ እንደሚወጣ በመጽሔቱ ሽፋን ተጽፎ ይገኛል ፡፡ ነገር ግን የሚወጣው በሶስትና በሁለት ወሮች ነው ለምን?

፱ኛ/ በኢ·ኦ·ተ·ቤ· ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ አማካኝነት መንፈሳውያንና ዘመናውያን መዝሙሮችን ትምህርቶች በካሴት እንደሚቀርጽ ከመጽሔቱ ተረድቻለሁ፡፡ ስለዚህ ስለ ትምህርቶቹና ስለ ካሴቶች የማስተዋወቅ ሙከራ ቢደረግ ምን ይመስላችኋል? ፡፡

ፍስሐ በሻሕ
ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
አራት ኪሎ

### መልስ

ፍሥሐ በሻሕ መንፈሳዊውን ሰላምታ ስላቀረብክልን እኛም ሰላምታችንን እናቀርባለን ፡፡ ከዚህም ቀጥለን ያቀረብካቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን ፡

፩ኛ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጸሎት የምትሰጠው መንፈሳዊ ምክር ምእመናን ሁሉ ከቂም ከበቀል እንደዚሁ ከመሳሰሉ ነገሮች ተጠብቆ ንጽሕና በተሞላበት መንፈስ መጸለይ ነው ፡፡

ዓይንን መጨፈን ያስፈልጋልን? ስለምትለው ግን ቤተ ክርስቲያን በጸሎት ጊዜ ዓይናችሁን ጨፍናችሁ ጸልዩ ብላ አታዝም ጽሑፍም የለም እንዲያውም አባቶቻችን ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት በሚጸልዩበት ጊዜ እንገታቸውን ወደ ሰማይ ቀና አድርገው ይጸልዩ እንደነበር ፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተዘግቧል ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አምስቱን እንጀራ አበርክቶ ለአምስት ሺ ሰዎች በመገበበት ወቅት "ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባርኮ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ይላል ማቴ· ፲፬–፲፱ ስለዚህ እጅን ዘርግቶ ወደ ሰማይ እንጋጠ መጸለይ እንጂ ዓይንን መጨፈን አስፈላጊ አይደለም ፡፡

፪ኛ ካህናት በሚይዙት የእጅ መስቀል ሥር ፬ መዓዘን የሚደረግበት ስለምንድን ነው የምን ምሳሌ መሆኑን እንድትገልጹልኝ ስለምትለውም ፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሕዝቡ ከኃጢአት የሚጠበቁበትና አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚፈጽሙበት በሙሴ አማካይነት ሕጉና ስሙ የተጻፈበት ፬ መዓዘን ያለው ጽላት ለምእመናን እሥራኤል ተሰጠ የዚሁም አሠራር የጽላቱ ምሳሌ ነው ዘጸ አ ፴፪–፲፭ ፡፡ በኋላ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በ፬ መዓዝና ዓለም የነበረውን ሕዝብ ማዳኑ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ወበእንተ ኃጣውኢነ ውእቱ ተሰቀለ ዲበ ዕፅ (ስለ እኛ ኃጢአት እሱ) ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቀለ ሲል አረጋግጦ ጽፎ እናገኘዋለን ፩ኛ ጴጥ· ፪–፳፬ ፡፡

፫ኛ/ የቅዱስ ጳውሎስ ትውልድና ነገዱ የት ነው ላልከው ፡ ትውልዱ አይሁዳዊ ነገዱ ከነገደ ብንያም ነው የሐዋር· ሥራ ፳፩ ፳፫ ፳፪–፫ ፡፡

፬ኛ/ የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን እምነት ልዩነቱ ምንድነው? ስላልከው ሰዱቃውያን ትንሣኤ ሙታን መልአክ (ነፍስ) መንፈስ የለም ባዮች ሲሆኑ ፈሪሳውያን ግን ትንሣኤ ሙታን መልአክ ነፍስ መንፈስ መኖሩን ከማመናቸውም በላይ ከትንሣኤ በኋላም ተጋብተን ቤት ትዳር መሥርተን

(ወደ ገጽ ፫ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ከአካል ክፍሎች አንዱ ቢታመም ሁሉም ይሠቃያሉ

ለአንድ ዛፍ ሥሮች ጫፎች ቀጠሎች አበባዎችና ፍሬዎች ይኖሩታል ይሁን እንጂ ለሁሉም ሥራቸው
አንድ ሳይሆን የተለያየ ነው ሥሮቹ ከመሬት የአፈር ምግብን ይስባሉ ቅርንጫፎች ከወደላይ ጠልን ይነሣሉ
ከሁሉም አቀጣጫ የሚተላለፋትን ምግቦች ግንድ በመቀበል ሁሉም በየአሉበት ጸንተው ሥራቸውን በሚገባ
እንዲያከናውኑ ያደርጋል ፡ ይህ ካልሆነ ዛፉ ልምላሜ ሊኖረውና ፍሬን ሊያፈራ አይችልም በመጀመሪያ
ይጠወልጋል ። ከዚያም ቀጥሎ ይደርቃል ከደረቀም በኋላ ተነቃቅሎ ድሬሽ ይጠፋል ።

የሰውን ሕይወት በዛፍ መስለን ልንናገረው እንችላለን ሰው አንድ አቋም ያለው ይሁን እንጂ በሰውነቱ
ውስጥ ብዙ የተለያዩ የአካላት ክፍሎች አሉት አካላቱ ስማቸውም ሥራቸውም የተለያየ ነው ሁሉንም
በየስማቸው እየጠራን የእያንዳንዱን ሥራ በዝርዝር ለመግለጽ ብንሞክር ብዙ ዓምዶችን ያስፈልገናል ።
ስለዚህ ከስማቸውም ከሥራቸውም በመጠኑ እንመለከታለን ።

ስለዚህ ከስማቸውም ከሥራቸውም በመጠኑ እንመለከታለን ።
ስለዚህ ከስማቸውም ከሥራቸውም በመጠኑ እንመለከታለን ። ስለዚህ ከስማቸውም ከሥራቸውም በመጠኑ እንመለከታለን ።

ዓይን ያያል ጆሮ ይሰማል ፡ አፍንጫ ያሸታል አፍ ይናገራል ልብ ያስባል እግር ይራመዳል እጅ
ይዳስሳል ሌሎችም ስማቸው ያልተጠራ የአካል ክፍሎች የተመደበላቸውን ሥራ ከመሥራት አያቋርጡም
ስለአካላት የሥራ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ከጻፈው መልእክት እንመለከት "አካል
የተሠራው ከብዙ አካል ክፍሎች ነው እንጂ ከአንድ የአካል ክፍል ብቻ አይደለም እግር እኔ እጅ ስላልሆንሁ
የአካል ክፍል አይደለሁም ቢል እንዲህ በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ አይቀርም አካል በሙሉ ዓይን ብቻ
ቢሆን ኑሮ የመስማት ሕዋስ የት በሆነ ነበር? አካል በሙሉ ጆሮ ብቻ ቢሆን ኑሮ የማሽተት ሕዋስ የት በሆነ
ነበር? አሁን ግን እግዚአብሔር እንደፈለገው እያንዳንዱን የአካል ክፍል ተገቢ ስፍራውን ይዞ እንዲገኝ
አድርጎታል አካል የተሠራው ከአንድ የአካል ክፍል ብቻ ቢሆን ኑሮ ሙሉ አካል የት በተገኘ ነበር ፡ አሁን ግን
ብዙ የአካል ክፍሎች ቢኖሩም አካል ግን አንድ ብቻ ነው ይልና ዓይን እጅን አንተ አታስፈልገኝም ሊለው
አይችልም ራስም እግርን አንተ አታስፈልገኝም ሊለው አይችልም እንዲሁም ደካሞች መስለው የሚታዩ
የአካል ክፍሎች ይበልጥ አስፈላጊዎች ናቸው አነስተኛ ክብር ያላቸው መስለው ለሚታዩን የአካል ክፍሎች
ይበልጥ ክብር እንሰጣቸዋለን የሚያሳፍሩ መስለው የሚታዩንን የአካል ክፍሎች ይበልጥ እንጠነቀቅላቸዋ
ለን እግዚአብሔር ግን የሚያሳፍሩ መስለው የሚታዩንን የአካል ክፍሎች በበለጠ ክብር እንዲያዙ አድርጎ
አገጣጥሟቸዋል ይህንንም ያደረገው በአካል ክፍሎች መካከል መለያየት ሳይኖር እርስ በእርሳቸው
እንዲተሳሰቡ ነው ።

እንዲተሳሰቡ ነው ። እንዲተሳሰቡ ነው ። እንዲተሳሰቡ ነው ።

አንዱ የአካል ክፍል ሲሠቃይ ሌሎችም የአካል ክፍሎች በሙሉ አብረው ይሠቃያሉ አንዱ የአካል
ክፍል ሲከበር ሌሎቹም የአካል ክፍሎች አብረው ከእርሱ ጋር ይደሰታሉ ። ይላል ፩ኛ ቆሮ ፲፪-፲፬ ፳፯ ።
ሐዋርያው በአካል ክፍሎች መስሎ ያስተማረው የሰው ወገን ለሆነ ሁሉ ነው አካላት በመተባበር ሰውን
ሰው አሰኝተውት እንደሚኖሩ ምእመናንም በክርስቶስ ስም አምነው በሚሠሩት መልካም ሥራ
እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙታል ። በስመ እግዚአብሔር አምነው የተጠመቁ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር አንድ
ሁነዋልና በመካከላቸው ወንድ ሴት ሽማግሌ ወጣት ትንሽ ትልቅ ነጭ ጥቁር የሚል አስተሳሰብ ሊኖር
አይገባም የሐ. ሥራ ፬ ፴፩ ፴፯ እንደምንመለከተው ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ ያላቸውንም ሁሉ
አንድነት አደረጉ መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር
በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተተ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በንጹሕ ልብ
ምግባቸውን ይመገቡ ነበር ይላል ።

ይህንን ቃል የተገነዘቡ ክርስቲያኖች ብቻቸውን እየበሉና እየጠጡ ከመደሰት ይልቅ ከጦም አዳሪዎች
ጋር አብሮ መብላት መጠጣት ያስደስታቸዋል ። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የኢትዮጵያን
ምእመናን ለመርዳት የሚለግሰው የእህልና የልብስ ርዳታ ለተጠቀሰው ቃል በቂ መረጃ ሊሆን ይችላል ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ምእመናንም በድርቅና በሰው
ሠራሽ ችግር የሚሠቃዩት ወገኖች የሥጋቸው ቁራጮች የአጥንታቸው ፍላጮች መሆናቸውን በመገንዘብ

በተናጠል በየጊዜው ... በመስጠት ላይ ይገኛሉ ።
ከሰለት ጉርሳቸው ከዓመት ልብሳቸው እየከፈሉ በመስጠት ላይ ይገኛሉ ። በተናጠል በየጊዜው
ከሚለግሡት ሌላ ከሚያዝያ ፳-፳ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ ም በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት ለጸሎትና
ለስግደት ከተሰበሰቡት ምእመናን አስተዋጽኦ እንዲጠየቅ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በሰጡት መንፈሳዊ መመሪያ መሠረት በርከት ያለ ገንዘብ ተዋጥቶ
ለተረጅ ወገኖቻችን በፍጥነት እንዲደርሳቸው ተደርጓል ።
ለተረጅ ወገኖቻችን በፍጥነት እንዲደርሳቸው ተደርጓል ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋን የሚያሰጥ በመሆኑ ችግሩ

እንደዚህ ያለው በጎ አድራጎት ከእግዚአብሔር ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋን የሚያሰጥ በመሆኑ ችግሩ
እስከሚወገድ ድረስ ያለ ማቋረጥ መቀጠል ይኖርበታል ። ምእመናን መማርና ማወቅ ብቻ ሳይሆን
የተማሩትንና ያወቁትን በሥራ መተርጐም ይገባቸዋል ።
የተማሩትንና ያወቁትን በሥራ መተርጐም ይገባቸዋል ። ደስ ይበላችሁ ከሚያለቅሱ ጋር አልቅሱ" እንዳለው

ሐዋርያው ጳውሎስ "ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ከሚያለቅሱ ጋር አልቅሱ" እንዳለው
ሐዋርያው ጳውሎስ "ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ... ከሚያለቅሱ ወገኖች ጋርም የችግራቸው
ከደስተኞች ሰዎች ጋር መደሰት ብቻ ሳይሆን ከፍቷቸው ለዝነው ከሚያለቅሱ ወገኖች ጋርም የችግራቸው
ተካፋይ በመሆን ማልቀስ ይገባል ። ወገኖቻችን እያለቀሱ እኛ መሣቅ ወገኖቻችን እየተራቡና የተጠሙ እኛ
ያለልክ መብላትና መጠጣት አይገባንም ችግሩ ከወገኖቻችን እስከተወገደ ድረስ ከእነርሱ ጋር መቸገር
ይገባናል ።

ሌሊትና መዓልት ተፈራራቂዎች በመሆናቸው ሌሊቱ እንደጨለመ ፡ መዓልቱም ብርሃን እንደሆነ
አይኖርም እንደዚህም ሁሉ እነዚሁ አሁን በችግርና በመከራ ማዕበል ተውጠው የሚጨነቁት ወገኖቻችን
አንድ ቀን ከችግር ለዘቅት ወጥተው በደስታ ባሕር የሚዋኙበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።
አንድ ቀን ከችግር ለዘቅት ወጥተው በደስታ ባሕር የሚዋኙበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ። አንሥቶ ጥሎ ወገኖቻችን ከጭንቀት ነፃ

አሁን በወገኖቻችን ላይ የወደቀውን የመከራ ቀንበር አንሥቶ ጥሎ ወገኖቻችን ከጭንቀት ነፃ
ለማድረግ ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ መተባበር ይኖርበታል ። እጁን ወይም እግሩን ወይም ታናሽ ጣቱን የታመመ
ሰው ሙሉ ጤንነት እንደማይሰማው የድርቅና የሰው ሠራሽ ችግሮች ከምድረ ኢትዮጵያ ካልተወገዱ
ኢትዮጵያውያን ጤናማ ኑሮ ለመኖር እንደማይችሉ የተረጋገጠ ነው ። ስለዚህ እየተዛዘንና እየተረዳዳን
ኢትዮጵያውያን ጤናማ ኑሮ ለመኖር እንደማይችሉ የተረጋገጠ ነው ። ስለዚህ እየተዛዘንና እየተረዳዳን
ኢትዮጵያውያን ጤናማ ኑሮ ለመኖር እንደማይችሉ የተረጋገጠ ነው ። ስለዚህ እየተዛዘንና እየተረዳዳን
ሰላምን ፍቅርን አንድነትን እንዲሰጠን አምላካችን እንለምነው ።
ሰላምን ፍቅርን አንድነትን እንዲሰጠን አምላካችን እንለምነው ። የማይነሣ ሁሉን ለማድረግ የሚችል ነውና ።

አምላካችን ቸርና ርኅሩኅ የነገሩትን የማይረባ የለመኑትን የማይነሣ ሁሉን ለማድረግ የሚችል ነውና ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፭ የዞረ)

እንኖራለን ይላሉ ልዩነታቸውም
በዚህ ነው ።

፫ኛ/ ስቆቃወ ኤርምያስን የጻ
ፈው ራሱ ኤርምያስ ነው ። ዕዝ
ራም ነው ይላሉ ።

፬ኛ/ በጾም ጊዜ በቤተ ክርስቲ
ያናችን ሕግና ሥነ ሥርዓት ደም
የሚወጣው ሁሉ አይበላም በማ
ለት ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፭
ስለ ጾም ምግቦች ሲገልጽ ወእለ
ይጸውሙ እስከ ፍጻሜ መዓልት
ወኢይት በላዕ በሙ እንስሳ ዘይወ
ጽእ እምኔሁ ደም ይላል እንዲህም
ማለት እነዚህ አጽዋማት ሙሉ
ቀን ይጾማሉ በሚጾሙበትም ጊዜ
እንስሳ ሁሉ አይበላባቸውም
ይላል ።

፺ኛ ሥርዓተ ተክሊል ከተፈ
ጸመ በኋላ ሥጋውን ደሙን መቀ
በል ነው ።

፰ኛ የትንሣኤ መጽሔት እር
ግጥ ከዚህ በፊት በወር አንድ ጊዜ
፪ሺ ብቻ ይታተም ነበር ። አሁን
ግን በሁለት ወር እንዲታተም
የተደረገው በ፪ሺ ኮፒ የነበረውን
፺ሺ እንዲሆን በየሁለት ወሩ እን
ዲታተም በመወሰኑ ነው እንጂ
በሌላ አይደለም ።

፱ኛ በኢ.ኦ.ተ.ቤ. ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ
ተልዕኮ መምሪያ አማካኝነት መን
ፈሳውያንና ዘመናውያን መዝሙ
ሮች ሌሎችም ትምህርቶች በካ
ሴት እንደሚቀረጹ ከመጽሔቱ
ተረድቻለሁ ። ስለዚህ ስለ ትምህ
ርቶቹና ስለ ካሴቶች የማስተዋ
ወቅ ሙከራ ቢደረግ ምን ይመስላ
ችኋል ስለምትለውም ራሱ መጽ
ሔቱ እያስተዋወቀ ነው ። ምክንያ
ቱም በሽፋኑ ተገልጾ ተጽፎአል
ሌላ ማስተዋወቅ የሚያስፈልገው
አይመስለንም ።

ክነፈ ርግብ ማርቆስ

## ጋብቻና ...

(ከገጽ ፲፪ የዞረ)

የግብረ ሥጋ ግንኙነት አባት
አልባ የሆነ ልጅ እየተወለደ ያለአ
ባት ቁጥጥር በሴትኛ አዳሪ የተበ
ላሸ ኑሮ መካከል የሚወለደው
ሁሉ የክፉ ነገር ጆሮ ጠገብ ሆኖ
ስለሚያድግ ባህርይው የተበላሸ
የኅብረተሰብእ ጠንቅ የሆነ አደ
ገኛ ቤተሰብእን የሚፈጥር ይሆ
ናል ።

አፈወርቅ አሰገድ





www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የትንሣኤን በዓል ምክንያት ማድረግ ያስተላለፉት ቃለ ቡራኬ

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን



ቅዱስነታቸው ቃለ ቡራኬ ሲያስተላልፉ

በአሁኑ ሰዓት በከተማና በገጠር ፣ በጠረፍና በመሐል አገር የምትገኙ ኢትዮጵያን እንዲሁም የሀገርን አንድነት ፣ የወገንን ደኅንነት ለመጠበቅ በየክፍሉ ያላችሁ ወገኖቻችን ፣ በሕመም ምክንያት በቤታችሁና በየሆስፒታሉ ያላችሁ ሁሉ ፤

ለሰው ልጆች ቤዛ ሆኖ በመስቀል ላይ የሞተውና ሞትን ድል አድርጎ በሶስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በአምላካዊ ሥልጣኑ የተነሣው የሰላም አምላክ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ ።

"አማን ተንሥአ እግዚእነ"

ጌታችን በእውነት ተነሥቶአል (ሉቃ.፳፬፥፴፬)

በመሠረቱ የሰው ልጅ ሲፈጠር ለዘለዓለም በሕያውነት እንዲኖር ነበር ። ነገር ግን ሰይጣን በአመጣበት ፈተና ወደቀ ። ከእግዚአብሔርም ተለየ ። የቀድሞ ክብሩን አጣ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በፈታሒነቱ አንፃር መሐሪነቱ ያለና ሰውንም የሚወድ በመሆኑ ፣ ሰው ከማዕርጉ እንደተዋረደ ፣ ከክብሩ እንደተለየና ከገነት እንደወጣ እንዲቀር አልፈቀደም ። በዚህም ምክንያት ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድ የባሕርይ ልጁን እግዚአብሔር ወልድን ወደ ዓለም ላከው። እግዚአብሔር ወልድም ከቅድስት ድንግል ማርያም ነፍስና ሥጋን ተዋህዶ ሰው ሆኖ በመወለድ ለዓለም ሁሉ ቤዛ ይሆን ዘንድ በመስቀል ተሰቀለ ሞተ ተቀበረ ። በሶስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ይህንም ወንጌላዊው በአማን ተንሥአ እግዚእነ ጌታችን በእውነት ተነሥቶአል በማለት የትንሣኤውን እውነተኛነት አረጋግጦአል ።

በክርስቶስ ትንሣኤ የሰው ልጆች ሁሉ ትንሣኤ ተረጋግጦአል ። ከሞት በኋላም ሕይወት መኖሩ ታውቆአል ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ጠቅሶ ሲናገር "ሞት ሆይ! ማሸነፍህ የት አለ? መቃብር ሆይ! ድል አድራጊነትህ ወዴት ነው? ክርስቶስ ተነሥቶአልና በትንሣኤውም ለሙታን ሁሉ የትንሣኤን መሠረት አኑሮአል" በማለት የሁላችን ትንሣኤ በክርስቶስ ትንሣኤ የተረጋገጠ መሆኑን አስረድቷል ።

የክርስቶስ የትንሣኤው በዓል የበዓላት ሁሉ በኩር ነው ። ምክንያቱም የማዳን ሥራው ሁሉ የተፈጸመበት ፣ ደቂቀ አዳም ከግብርናተ ዲያብሎስ ነፃ የወጡበት ፣ ከፈጣሪያቸው ጋር የታረቁበት ፣ አጥተውት የነበረውን የጸጋ ልጅነት መልሰው ያገኙበትና ወደቀደመ ቦታቸው የተመለሱበት ስለሆነ ነው ።

እንዲሁም የቀድሞው በደል ማለት ሞተ ነፍስ የተወገደበት አዲሱ ዘለዓለማዊው ሕይወት የተጀመረበት በመሆኑ በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከፍተኛና ልዩ ክብር የሚሰጠው የበዓላት ሁሉ በኩር ነው ።

የትንሣኤ በዓል ከላይ እንደተገለጸው ሞተ ነፍስ ፣ መከራ ነፍስ የተወገደበት ፣ ድኅነተ ነፍስ የተገኘበት ፣ ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩ የተረጋገጠበት ስለሆነ በፍጹም መንፈሳዊ ደስታ የሚከበር መንፈሳዊ በዓል ነው ።

በክርስቶስ ሞት ምክንያት አዝነውና ፈርተው በዝግ ቤት የነበሩ ሐዋርያት ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን ክርስቶስን በአዩት ጊዜ እጅግ ደስ ብሎአቸዋል ። መጽናናትንም አግኝተዋል። የነበረባቸውም ፍርሃት ተወግዶላቸው ጌታ በእውነት ተነሥቶአል እያሉ ትንሣኤውን ለመመስከር ችለዋል።

የክርስቶስ ትንሣኤ የመንፈስ ነፃነትንና እውነተኛ ሰላምን የሚሰጥ የሰላም በዓል ነው ። ክርስቶስ በሞተ ጊዜ ሐዋርያት የሕሊና እረፍትና ሰላም በማጣት በፍርሃትና በተቢዐ ተስፋ ተይዘው በዝግ ቤት ሳሉ ክርስቶስ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" በማለት በመካከላቸው በተገለጠ ጊዜ ዓለም ሊሰጠው የማይችለውን ሰላም እውነተኛ ሰላም አግኝተዋል ። ይህም ሰላም ለእነሱ ብቻ ሳይሆን በእነሱ በኩል ሊቀበለው ለሚፈልግ ሁሉ የተሰጠ ዘለዓለማዊ ሰላም ነው ።

ይህ ዘለዓለማዊ ሰላም ዛሬ ለእለንበት ዓለም እጅግ ያስፈልገዋል። የሞት መሣሪያዎች ሁሉ ለሕይወት ማዳኛ አገልግሎት እንዲውሉ ፣ በዓለም ውስጥ ጦርነት ጠፍቶ ለጦርነት የሚወጣው ገንዘብ ሁሉ ለዕድገት ለብልጽግና አንዱ ሀገር ከሌላው ሀገር ጋር ለሚስተካከልበት ዓላማ እንዲውል ለማድረግ ሰላም አስፈላጊ ነው ።

ስለ ሰላም መስለፍና መጮህ የሚያስፈልጋቸውም ሰላምን ያጡ ብቻ ሳይሆኑ ለጊዜው በአካባቢያቸው ሰላም ያለ የሚመስላቸው ሁሉ ሰላም ያጡ ወገኖች ሰላምን ስለሚያገኙበት ሁኔታ መተባበርና ሰላም በሁሉም እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

ዓለማችን በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ ምክንያት ከሚመጡ ልዩ ልዩ ችግሮች ከአባር ፣ ከቸነፈር ፣ ከጦርነትና ከመሳሰሉት ሁኔታዎች አንፃር ወደፊት ያለው ሕይወቱ ጨልሞ እየታየው በከፍተኛ ፍርሃትና ጭንቀት ላይ ሆኖ ይታያል ። እንዲሁም በየአካባቢው ከሚሰማው የጦርነትና የጦር መሣሪያዎች ብዛት የተነሣ በሥጋት ላይ ይገኛል ። እንደዚህ ባለ ችግር ፍርሃትና ጭንቀት በሚገኘው ዓለም ሰላምን ለመመሥረት በሕዝቦች መካከል ወንድማማችነትንና መተባበርን ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረትን በማድረግ ላይ የሚገኙትን ሁሉ ከሙታን ተለይቶ የተነሣውና ለሐዋርያት ሰላም ለእናንተ ይሁን በማለት ሰላምን የሰጣቸው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲረዳቸውና ጥረታቸውን ለእውነተኛ ሰላም እንዲያበቃላቸው አብያተ ክርስቲያናትና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሁሉ አዘውትረው ሊጸልዩ ይገባል ።

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን ካህናትና ምዕመናን!

ዛሬ ከሞት ወደ ሕይወት ፣ ከሐሣር ወደ ክብር ከጨለማ ወደ ብርሃን የተሸጋገርንበትን የጌታችንና የመድኃኒታችንን በዓለ ትንሣኤ የደስታና የሰላም በዓል መሆኑን በማብሰር ስናከብር ልናስበውና ልንፈጽመው የሚገባን ዐቢይ ጉዳይ አለ ። ይኸውም በአገራችን ሰሜናዊ ክፍል በተለያዩ ቦታዎች በአለው ችግር ምክንያት ከቤትንብረታቸው ተፈናቅለው መጠለያና የዕለት ምግብ እስከማጣት ደርሰው በከፍተኛ ችግር የሚገኙ ወገኖቻችን መኖራቸው ነው ። ስለሆነም እግዚአብሔር በቸርነቱ ለሀገራችን ሰላ




www.ethiopianorthodox.org

# ሰላሜን እሰጣችኋለሁ

## ይህ ቃል የጌታችን መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው

**ሰላም ማለት በስምምነትና በአ
ንድነት አብሮ መኖር ማለት
ነው። ደግሞም የእረፍት ስሜት
ነው ። ሰዎች ሲገናኙ የሚለዋወ
ጡት የሰላምታ ቃል ወይም የንግ
ግር መክፈቻ ቃል ነው ።**

ምን፡ ፍቅር አንድነትን እንዲሰጥ
ልንና ወደ የአካባቢያቸው ተመል
ሰው ሰላማዊ ኖሮአቸውን አድ
ሰው ለመኖር እንዲችሉ አዘውት
ረን መጸለይ ፡ እስከዚያም ድረስ
የችግራቸው ተካፋይ በመሆን
ማድረግ የሚገባውን ነገር ሁሉ
በማድረግ ከነዘናቸው ልናጽናና
ቸውና ልናረጋጋቸው ይገባል ።

ከሙታን ተለይቶ የተነሣው
ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ለእናንተ
ሊያደርጉላችሁ የምትሹትን ሁሉ
እናንተም ለሌሎች አድርጉላ
ቸው" የሚለው ትምህርት ይህ
መሆኑን ከልብ መገንዘብ ይገባ
ናል ።

እኛ በቤታችን በዓል ስናደርግ
ከቤተሰቦቻችን ጋር ደስ ሲለን
ለእነርሱም ይህ ሁሉ እንደሚያስ
ፈልጋቸው ማስተዋልና ለዚህም
ትብብር ማድረግ ክርስቲያናዊ
ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈል
ጋል ።

የሰላም አምላክ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ለሀገራችን ሰላምን ፡ አንድነ
ትንና ፍቅርን ፡
ለአዘኑ መጽናናትን ፡
ለተቸገሩ ረድኤትን ፡ ለታመሙ
ጤንነትን ፡
ለሙታን መልካም ዕረፍትን ይስ
ጥልን
ለዓለምም ሁሉ ሰላምን ያድልልን
በዓሉን የሰላም የደስታ በዓል ያድ
ርግልን ።

አሜን ።

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፳
ከቁጥር ፲፱ እስከ ፳፫ እንመልከት፡
ያን ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተ
ኛው በመሸ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ
ተሰብስበው በነበሩበት አይሁድን
ስለፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየ
ሱስ መጣ በመካከላቸውም ቆሞ
ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው
ይህንንም ብሎ እጆቹንም ጎኑንም
አሳያቸው ደቀመዛሙርቱም ባዩ
ጊዜ ደስ አላቸው ኢየሱስም ዳግ
መኛ ሰላም ለእናንተ ይሁን አብ
እንደላከኝ እኔም ደግሞ እልካችኋ
ለሁ አላቸው ይህንንም ብሎ እፍ
አለባቸው መንፈስ ቅዱስን ተቀ
በሉ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋ
ቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል ። የያዛች
ሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።
እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ሰው
በክርስቶስ አምኖ ከኃጢአቱ
ነጽቶ ከእግዚአብሔር ጋር ሲታ
ረቅ ነው ። የሮሜ መልእክት
ምዕራፍ ፭ ከቁጥር ፩ እስከ ፬

እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን
በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ
በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት
ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን
አግኝተናል ። በእግዚአብሔር
ክብርም ተስፋ እንመካለን ። ወደ
ኤፌሶን ምዕራፍ ፪ ከቁጥር ፲፬
እስከ ፲፯ ።

እራሱ ሰላማችን ነው ሁለቱን
ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም
የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል
ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው
ያፈረስ ይህም ከሁለታችን አን
ድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር
ዘንድ ሰላምን ያደርግ ዘንድ
ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ
ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግ
ዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ
ነው ።

መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ
ለእናንተ ሰላምን ፡ ቀርበው ለነበ
ሩትም ሰላምን የምሥራች ብሎ
ሰበከ ። ሰላም የመንፈስ ፍሬ ነው።
ወደ ገላትያ ምዕራፍ ፭ ከቁጥር ፳፪
እስከ ፳፮ የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር
ደስታ ሰላም ትእግሥት ቸርነት
በጎነት እምነት የዋኅነት ራስን
መግዛት ነው እንዲሁ ያሉትን
የሚከለክል ሕግ የለም ። የክርስ
ቶስ ኢየሱስም የሆኑት ሥጋን
ከክፉ መሻትና ከምኞቱ ጋር
ሰቀሉ ። በመንፈስ ብንኖር በመን
ፈስ ደግሞ እንመላለሳለን እርስ
በርሳችን እየተነሳሳንና እየተቀና
ናን በከንቱ አንመካ ። እግዚአብ
ሔር ለሚታመኑት የራሱን ሰላም
ይሰጣቸዋል ። ት ኢሳይያስ ምዕ
ራፍ ፳፮ ቁጥር ፫ ፡ ፬ ፡ በአንተ
ለምታምን በአንተ ለምትደገፍ
ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃ
ታለህ እግዚአብሔር የዘለዓለም
አምባ ነውና ለዘለዓለም በእግዚአ
ብሔር ታመኑ ዮሐንስ ም·፲፬
ቁጥር ፳

ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላ
ሜን እሰጣችኋለሁ ፡ እኔ የምሰጣ
ችሁ ዓለም እንደሚሰጠው አይደ
ለም ልባችሁ አይታወክ አይፍ
ራም ።

ወደ ፊልጵስዩስ ምዕራፍ ፬
ቁጥር ፯ እና ፯ በነገር ሁሉ በጸሎ
ትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግ
ዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን
አስታውቁ እንጂ በአንዳች አት
ጨነቁ ። አእምሮንም ሁሉ የሚያ
ልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባች
ሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየ
ሱስ ይጠብቃል ።

በቀረውስ ወንድሞች ሆይ እው
ነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ጭምት
ነት ያለበትን ነገር ሁሉ ጽድቅ
የሆነውን ነገር ሁሉ ፍቅር ያለበ
ትን ነገር ሁሉ መልካም ወሬ
ያለበትን ነገር ሁሉ በጎነትም
ቢሆን ምስጋናም ቢሆን እነዚህን
አስቡ ፡ ከእኔ የተማራችሁትንና
የተቀበላችሁትንና የሰማችሁትን
እነዚህን አድርጉ ። የሰላምም አም
ላክ ከእናንተ ጋር ይሁን ። ሮሜ
ምዕራፍ ፲፪ ቁጥር ፲፰

ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል
ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ ፩ኛ
ጴጥሮስ ምዕራፍ ፫ ፡ ቁጥር ፲፩

ሕይወትን ሊወድ መልካሞች
ንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው
ምላሱን ከክፉ ከንፈሮችንም ተን
ኰልን ከመናገር ይከልክል ።
ከክፉ ፈቀቅ ይበል መልካምንም
ያድርግ ሰላምን ይሻ ይከተላትም ፡
የጌታ አይኖች ወደጻድቃን ናቸ
ውና ፡ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው
ተከፈተዋል ። የጌታ ፊት ግን ክፉ
ነገርን በሚያደርጉ ላይ ነው ።

ከዚህ በላይ የተገለጸው ቃል
የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን
ጊዜም ቢሆን ለሰው ልጅ ሰላም
አስፈላጊ መሆኑን ነው በዚህ
ዓለም የምንኖርበት ዘመን አጭር
መሆኑ ይገባናል እግዚአብሔር
በመካከላችን መኖሩን የምናወ
ቅው እርስ በርሳችን በፍቅርና
በሰላም ተግባብተን ስንኖር ነው
እግዚአብሔር ፍቅር ነው ተብሎ
ተጽፎአል ።

የሰላም አምላክ እግዚአብሔር
ሰላምን እንዲሰጠን በጸሎት ዘወ
ትር እንለምነው

_ጋምጎፋ ሀ/ስብከት
መምሬ ሽታ ከበደ_

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለው ኑፋቄ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ፈቃድ አለው በሚል መሠረተ ሃይማኖት ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀው የእርቅ ሰነድ ።

ከመ ሉሉ መልአክ

ከዮስጢንያኖስ በኋላ ከነገሡት
ከቢዛንታይን ንጉሥ ከአጼ ሕር
ቃል (፳፻፴፭—፮፻፵፩ ዓ·ም)
ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በግብጽ
የኮፕቶች (የተዋሕዶዎች) ኑሮ
የመረረ የሥቃይና የመከራ መቀ
በያ ሕይወት ሆኖ ነበር ።

በተከታታይ በፋርሶችና በአረ
ቦች ጦር በመከበቡ ምክንያት
የቢዛንታይን መንግሥት በተዳከ
መበት ወቅት በአፍሪካ ለነበረው
የቢዛንታይን ግዛት ጦር አዛዥ
ሕርቃል የሥልጣን ተቀናቃኞ
ቹን ደምስሶ እንደነገሠ በቾስሮ
ኤስ ፖርቪዝ የተመራው የፋርስ
ጦር በእስያ የቢዛንታይን መንግ
ሥት ቅኝ ግዛት ከነበሩት ሀገሮች
በ፮፻፲፫ ዓ·ም ሦርያን ፡ በ፮፻፲፬
ዓ·ም ኢየሩሳሌምን ይዞ ጌታ የተሰ
ቀለበትን ግማደ መስቀልና ሌሎ
ችንም ንዋያተ ቅድሳት ዘርፎ ወደ
ሀገሩ ወስዶ የፋርስ ጦር ሦርያንና
ፍልስጥኤምን በመያዝ ሳይወሰን
በ፮፻፲፱ ዓ·ም አንዱ ክፍለ ጦር
በቮስፈረስ የባሕር ሰርጽ በኩል
የቁስጥንጥንያን አካባቢ ሲወጋ
ሌላው ክፍለ ጦር ደግሞ የቢዛንታ
ይን መንግሥት ቅኝ ግዛት የነበረ
ችውን ግብጽን ወረረ ።

በዚያን ዘመን ኃያልና ሰፊ የነ
በረው የቢዛንታይን መንግሥት
በዜጎቹ መካከል ሰላም ማስፈን
ተስኖት በመዳከም ላይ በነበረበት
ወቅት ልበ ሙሉ ጀግና የነበረው
አጼ ሕርቃል በፋርሶች ላይ ዘምቶ
በ፮፻፳፪ ዓ·ም ድል አደረጋቸው
በምርኮ የወሰዱትንም ግማደ መስ
ቀል ወደ ኢየሩሳሌም መልሶ በክ
ብር ከነበረበት ከጌታ መቃብር
ላይ እንዲያርፍ አደረገ ።

ግብጽን ይዞ የነበረውንም የፋ
ርስ ሠራዊት ድል አድርጎ አበረረ
በዚህም ጀግንነቱና ግማደ መስቀ
ሉን በማስመለሱ የሕርቃል ዝና
በቤተ ክርስቲያንና በዓለም ታሪክ
ሲተረክ ይኖራል ።

ሕርቃል በታላቅ ጀግንነት ፋር
ሶችን ድል በማድረግ የግዛቶቹን
ነጻነት ካረጋገጠ በኋላ ቀደም ሲል
በተነሡት ነገሥታት በሃይማኖት
ልዩነት ሰበብ በዜጎቹ መካከል
የተፈጠረው ንትርክ ጥላቻና መከ
ፋፈል ለጠላቶቹ ለፋርሶች የብር
ታት ፡ ለቢዛንታይን መንግሥት
የውድቀት ምክንያት መሆኑን ተገ
ነዘበ ሆኖም በሃይማኖት የተለያዩ
ዜጎቹን በሚያቀራርብ ፍትሕን
በተከተለ መንገድ ለጠቡ እርማ
ትና መፍትሔ በመሻት ፈንታ
ከሱ በፊት የተነሡ ነገሥታት
ከሞከሩት የከፋ ፍጅት የፈጠረ
የእርቅ ሰነድ አዘጋጀ ። የኸውም
ቀደም ሲል በተመለከትነው አንዳ
ችም እርቅና ሰላም ሊያመርድ ባለ
መቻሉ ተኮላሽቶ (ከሽፎ) በቀ
ረው ሔኖቲኮን "በተባለው የስም
ምነት ሰነድ ምትክ ከቁስጥንጥን
ያው ፓትርያርክ ከአቡነ ሰርጌዮስ
ጋር በመመካከር" ለጌታችን ለኢ
የሱስ ክርስቶስ አንድ ፈቃድ



www.ethiopianorthodox.org

አለው "(ሞኖፊሲቲዝም) የሚለውን መሠረተ ሃይማኖት የግሪክ ኦርቶዶክስና የተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሁሉ ተቀብለው በመስማማት አንድነታቸውን መሥርተውና አጽንተው ሀገራቸውን ከጠላት እየተከላከሉ በሰላም እንዲኖሩ በማለት በ፮፻፴፰ ዓ·ም አወጀ ። ይህም አዋጅ የግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆኑ ነገሥታት በዜጐቻቸው መካከል ሰላምን አፍነው ለመግዛት እንዲያመቻቸው ያወጁት ስለሆነ ፡ የአንድ ባሕርይን (የተዋሕዶን) መሠረተ ሃይማኖት ስላላነሣና የኬልቄዶንንም ጉባኤ ስላላወገዘ ለግሪክ ኦርቶዶክሶች በማድላት ተዋሕዶዎችን የሚጫን ነው በማለት በግብጽና በሦሪያ ክፍላተ ሀገሮች ይኖሩ የነበሩ ተዋሕዶዎች ወዲያውኑ ተቃወሙት በተለይም በግብጽ የሚኖሩት ኮፕቶች የግሪኮችን ተንኮል ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ከነቅዱስ አትናቴዎስና ቄርሎስ የተማሩት ቀጥተኛ የተዋሕዶ ሃይማኖታቸው እንዳይፋለስባቸው በመስጋትና በመፍራት የዚህንኑ ሰነድ (ዐዋጅ) ዓላማ በጥብቅ ተቃውመዋል ። ሆኖም ይህንኑ ሰነድ የአንጾኪያው ፓትርያርክ አቡነ አትናቴዎስና (፮፻፳፩—፮፻፳፱) የሮሙ ፖፕ ቀዳማዊ ሐኖሪዮስ (፮፻፳፭—፮፻፴፰) ተቀብለውት ነበር ነገር ግን በሁለቱም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ ወዲያው ከካህናቶቻቸው ዘንድ ከፍ ያለ ተቃውሞ ደርሶባቸዋል ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ትንሽ ቆየት ብላ በ፮፻፹ ዓ·ም በተደረገችው በሁለተኛዋ የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ፈቃድ አለት ብላ ወስናለች ።

አጼ ሕርቃል ያቀረበው የእርቅ ሰነድ ተቀባይ ማጣቱን ቢገነዘብም ቅሉ በቢዛንታይን ግዛት ውስጥ በብዛት የስንዴና የተለያዩ እሕሎች ማምረቻና ጐተራ በነበረችው ግብጽ የሚኖሩ ኮፕቶች በውድም ሆነ በግድ ስምምነቱን ተቀብለው በሰላም እንዲኖሩ ለማድረግ ቆርጦ ተነሣ ይህንንም ዓላማውን በጭካኔ መንገድ ከግቡ ሊያደርስለት የሚችል ቆራጥና ጨካኝ ካህን በጥቁር ባሕር አካባቢ የምትገኝ የፋሲል ጳጳስ አቡነ ሲሩስ መሆኑን ተገነዘበ ስለዚህ ከግሪክ ኦርቶዶክስ (ከመለካውያን) እምነት ተከታዮች ጋር በመተባበር ቢፈቅዱ በውድ ፡ ባይፈቅዱ በግድ "አንድ ፈቃድ" በሚለው የእርቅ ሰነድ መሠረት የኬልቄዶንን የሁለት ባሕርይ እምነት ውሳኔ እንዲቀበሉ እንዲያደርግ በ፮፻፴፩ ዓ·ም በእስክንድርያ የመለካውያን ፓትርያርክና በመላ ግብጽ የቢዛንታይን መንግሥት እንደራሴ አድርጎ ሾመው ይኸው ጨካኝና ምሕረተ ቢሱ አቡነ ሲሩስም ወደ እስክንድርያ ተጉዞ በ፮፻፴፩ ዓ·ም ከደረሰ በኋላ በመንግሥት ሹማምንት ፡ በመለካውያን ካህናትና ምእመናን በመደገፍ በሰነዱ የሰፈረውን ተቀብለው ከመለካውያን ጋር አንድ እንዲሆን ኮፕቶችን ቢጠይቃቸው ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ በመሆኑ መለኮትና ትስብእት ያለመለየት ፡ ያለመቀላቀል ያለመለወጥ ስለተዋሐዱ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አንድ ፈቃድ አንድ ግብር መሆኑን በምናምነው መሠረት አሁን ለክርስቶስ አንድ ፈቃድ አለው የሚለው ሰነድ ከመጀመሪያ ጀምሮ የተቀበልነው እምነት ቢሆንም ቅሉ ለሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መለያየት ዋነኛ ምክንያት የሆነው ክርስቶስ ሁለት ባሕርይ አለው የሚለው ኑፋቄ እስካልተወገዘ ድረስ ከቀጥተኛው የተዋሕዶ እምነታችን ዝንፍ አንልም ስላሉት ለአሥር ዓመታት ያህል የኮፕቶችን ካህናትና ምእመናን በመግረፍ ፡ በማሠር በመግደል ወዘተ .. ከፍ ያለ አሰቃቂ ሥቃይ ፈጸመባቸው እንዲሁም የካህናቱ የምእመናን ሀብትና የአብያተ ክርስቲያናት ንዋያተ ቅድሳት ተዘረፉ ። በበረሀ በሚገኙ ገዳማት መንነው የሚኖሩ መነኰሳትም ሰነዱን አንቀበልም ስላሉ በግርፋትና በሞት እንዲቀጡ አደረገ ። በዚያን ወቅት ስለ ተዋሕዶ እምነታቸው ሲሉ ሰማዕትነት ከተቀበሉት በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩት ካህናትና ምእመናን መካከል በእስክንድርያ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የቀዳማዊ ብንያም ወንድም ሚናስና በምንና ላይ የነበረው ባሕታዊ ሳሙኤል ይገኙባቸዋል ። የኮፕቶች ፓትርያርክ ቀዳማዊ ብንያም (፮፻፳፫—፮፻፷፪) ግን የቢዛንታይን መንግሥት መውደቂያና የዐረቦች ድል አድራጊነት እስከተቃረበበት ወቅት ድረስ ቴቤያድ ወደ ነበረው ገዳም ተሰዶ በመግባት እዚያው በብሕትውና ቆየ ኮፕቶች በደረሱባቸው ከፍተኛ ሥቃዮች ምክንያት በቢዛንታይን መንግሥትና በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነበራቸው ጥላቻና ቅሬታ ከጊዜ ወደ ጊዜ የባሰውን እየከረረ ሄደ ።

ስለዚህ ወዲያው የዐረብ ጦር የቢዛንታይንን መንግሥት በያለበት ከቦ ሲያስጨንቀው ኮፕቶች ቀደም ሲል በፋርሶች ወረራ ጊዜ ከግሪኮች ጐን በመሰለፍ ጠላትን ወግተው እንደመለሱ ሁሉ ዐረቦችንም ከግሪኮች ጐን ተሰልፈው ለመውጋት አልፈለጉም በቢዛንታይን መንግሥትና በግሪክ ኦርቶዶክስ (በመለካውያን) ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመባቸውን የሚያንገፈግፍ ጭፍጨፋ በማስታወስ በገለልተኝነት ከዳር ቆመው ጨቋኞቻቸው በነበሩት በቢዛንታይን መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰው ጥፋት ተገቢ ነው በማለት ዐረቦች የቢዛንታይንን ግዛት ግብጽን ድል አድርገው ሲይዙ ድርጊቱን የተቀበሉት በታላቅ ደስታ ነበር ።



# ዝናብን የምትጠጣ ምድር

የበላ ይጠግባል የጠጣም ይረካል ፡ ነገር ግን አንድ ጊዜ ምግቡን እንደጠገበ ሁል ጊዜ መኖር አይችልም ፡ ጠጥቶ የረካም ቢሆን ጠጥቼ አንድ ጊዜ ስለረካሁኝ መጠጥ አያስፈልገኝም አይልም ፡ ለብሶ የሞቀውም በለበሰው ልብስ እንደሞቀው አይኖርም ሰዓቱን እየጠበቀ ጊዜውን እያየ መመገብ፡ መጠጣት ፡ መልበስ የተለመደ ተግባር ነው ።

እግዚአብሔር አምላክ በዕለተ ፍጥረት በሦስተኛው ቀን "ለታብቍል ምድር ሐመልማለ ዘርዕ ዘይዘራዕ በበዓርአያሁ ወበበ አምሳሊሁ" ባለ ጊዜ በመጥረቢያ የሚቈረጡ ዕፀዋት (ዛፎች) በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕት በእጅ የሚለቀሙ አትክልት ከልምላሜ ፡ ከጽጌ ከፍሬ ጋር ለሥጋውያን ምግብ ሊሆኑ በምድር ላይ ተገኝተዋል ።

ከዚያ በኋላ የተለያዩ ወቅቶች ሆኑ በምድርም ፡ ላይ በአንድ ዓመት ውስጥ አራት የተለያዩ መልኮች ይታያሉ እነርሱም በሀገራችን በኢትዮጵያ ዘመነ ክረም ፡ ዘመነ መፀው ዘመነ ጸጋይ ፡ ዘመነ ፀደይ ፡ በመባል የታወቁ ናቸው ምድርም በተጠቀሱት ወቅቶች የተለያዩ መልኮችን ታሳያለች የምታሳየውም ኅብረ መልክዕ ወቅቶችን በመከተል ነው ።

ለምሳሌ በዘመነ ክረምት በአረንጓዴ ቅጠል ተሸፍና ትታያላች በዘመነ መፀው በአበባ ፍሬ ተሸልማ አጊጣና አምራ ስትታይ በዘመነ ጋጋይ ልምላሜዋንና አበባዋን አጥታ ፍሬዋን አስረክባ ፡ የዛፎች ቅጠሎች ረግፈው ሣሮች እምሽክ ድቅቅ ብለው ትቢያ ሆነው አቧራ ለብሳ አቧራዋ እንደ አመድ እየበነነ ትታያለች በዘመነ ፀደይ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ዝናብ ስለሚዘንብ በምድር ላይም ትንሽ ትንሽ ልምላሜ ይታያል ።

ዘመነ ክረምት ሦስት ወራትን የያዘ ሲሆን ቀኖቹ 90 ናቸው የሚጀመረው ሰኔ 24 ሆኖ የሚፈጸመው መስከረም 24 ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመንን አካባቢን እያየ በምሳሌ ማስተማር የተለመደ ተግባሩ ስለሆነ ከማያውቁት ምሳሌ ይልቅ በሚያውቁትና ከአጠገባቸው በሚገኘው ነገር እየመሰለ ቢያስተምሯቸው ለመረዳት እንደሚችሉ አውቆ ለነጋዴዎች በብር በወርቅ በዕንቁ ለገበሬዎች በዘር ለሴቶች በሊጥና በእርሾ ለእረኞች በበግና በፍየል በመንጋ ወዘተ እየመሰለ አስተምሯል ።

የሚቀጥለው ወቅት ክረምት ስለሆነ ጊዜውን የተመለከተ ምሳሌያዊ ትምህርት እንመለከታለን። "በዚህ ወቅት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤት ወጥቶ በባሕር ዳር ተቀመጠ ወደ ታንኳ ገብቶ እስከሚቀመጥ ድረስ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ ፡ ከሰው ብዛት የተነሣ ሕዝቡ ሁሉ በወደቡ ቆመው ነበር ። በዚያን ጊዜ ክርስቶስ የሚከተለውን ቃል በምሳሌ አስተማራቸው ። ምሳሌውም የሚከተለው ነው ።

"እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ወፎችም መጥተው በሉት ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ እሾህም ወጣና አነቀው ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ" ካለ በኋላ ዕዝነ ልቡና ያለው ያስተውል ብሏል ማቴ· ፲፫· ፩—፱ ።

በዚህ ምሳሌ አራት ዓይነት የአዝርዕት አወዳደቅን ተመልክተናል አዝርዕቶቹ አንድ ዓይነት ናቸው ገበሬውም የዘራቸው በእጁ እየዘገነ ነው ገበሬውና ዘሩ ያልተለያዩ አንድ ይሁኑ እንጂ ዘሩ የወደቀበት መሬት የተለያየ ይዞታ አለው ከላይ እንደተገለጸው አስተውሎ በመመልከት ለመረዳት ይቻላል ።

ምሳሌውን እንዲተረጉምላቸው ደቀ መዛሙርቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጠይቀውት እንደሚከተለው አብራርቶላቸዋል ። እንግዲህ እናንተ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ የወንጌልን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ ክፉው ይመጣል በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው ፡ በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ



www.ethiopianorthodox.org

ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው ፡ ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል ፡ በእሾህ መካከል የተዘራውም ቃሉን የሚሰማ ነገር ግን የዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት መቃለል ቃሉን ያንቃል የማያፈራም ይሆናል ። በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው እርሱም ፍሬን ያፈራል ፡ አንዱ ቅንጣት መቶ ስልሳ ሠላሳ ይሆናል ብሏቸዋል ።

ምድር ለፍጡራን መኖሪያ እንድትሆን መጠን ሥጋውያን ፍጡራንና ለእነርሱም የሚያስፈልጋቸውን ምግብ በየወቅቱ ታቀርባለች ይሁን እንጂ ምድር ብቻዋን የተሟላ አገልግሎትን ለፍጡራን ለማቅረብ አትችልም በዝናም አማካይነት ዕፅዋትን አዝርዕትን አትክልትን ታበቅላለች በነፋስ ታሳድጋለች በፀሐይ ታበስላለች ፡ እንደዚሁም ስለተባለ ዘሩ ከምድር ላይ ወድቆ ከአፈሩ ጋር ተገናኝቶ እንዴት እንደሚበቅልና እንደሚያድግ ለፍሬም እንደሚበቃ መርምሮ የሚያውቅ ጥበበኛ አይገኝም ይህንንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንግሥተ ሰማይ ምሳሌ አድርጎ በአስተማረበት አንቀጽ ሲገልጽ "በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል ፡ ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብልን ታፈራለች ፍሬው ግን ሲበስል መከር ደርሷልና ወዲያው ማጭድን ይልካል" ብሏል ።

በርእሱ እንደተገለጸው ምድር ዝናምን ተቀብላ የዘሩባትን እንደምታበቅል የተከሉባትን እንደምታጸድቅ የሰው ልጆችም በመምህራን አማካይነት በልባቸው የተዘራውን በጆሯቸው የፈሰሰውን ቃለ እግዚአብሔር በመልካም ሥራ አጉልተው የማሳየት ግዴታ አለባቸው ፡ መሬት የዘሩባትን ባታበቅል ዘረ ቆርጥም ተብላ መጨረሻዋ በእሳት መቃጠል እንደሆነ ሰዎችም ተምረውና ዓውቀው ሕገ እግዚአብሔርን ካልፈጸሙና ጥሩ ሥራ ካልሠሩ በመጨረሻ የሚጠብቃቸው በእሳተ ገሃነም መቃጠል ነው ፡ ከምሳሌው ከገኘነው ትምህርት በመረዳት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዙን ፈጽመን መንግሥቱን ለመውረስ እንበቃ ዘንድ በቸርነቱ ይርዳን ።

ሊ.ኅ. ልሣነ ወርቅ በዛብኅ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አድባራትና ገዳማት አካባቢ አብዛኛዎቹ ለልማት ሥራዎች አመች በመሆናቸው ብቃትና የሥራ ልምድ ያላቸው መነኮሳትና ካህናት ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር ደከመን ሰለቸን ሳይሉ የልማቱን ሥራ ተያይዘውት ይገኛሉ ።

በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩት አገልጋዮች ካህናት ከአለባቸው ችግር ሊገላገሉና ሊሻሻሉ የሚችሉት ከመንፈሳዊ አገልግሎት ሌላ በትርፍ ጊዜያቸው እንደ አካባቢው አስፈላጊነት እየታየና እየተጠና ለልማት ሥራ ተግትሮ ራሳቸውን አዘጋጅተው ከተገኙ ለአካባቢው ኅብረተሰብም ጭምር እንደሚረዱ ግልጽ ነው ።

ዛሬ በአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት በአብዛኛዎቹ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤቶች የቀሳውስትና የዲያቆናት መኖሪያ ቤቶች በማሠራት ሌላውንም የአብያተ ክርስቲያናቱን ውስጣዊ ጉድለት ከማሟላት አልፈው ዳቦ ቤቶች ልዩ ልዩ የተግባረ እድ (እደ ጥበብ) በማቋቋም ከሰው በታች የነበረውን የካህናት ኑሮ ያሻሻሉ ትጉሃን አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባኤ አባላት በመልካም አርአያነታቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል ።

የዚህ ዓይነቱን አሠራር ገና ያልጀመሩ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉም ሁላችን ስለምናውቅ "ባለቤት ከአልሮጠ ጐረቤት አይደርስም" የሚል የተለመደ አነጋገር ስለአለ የአድባራትና የገዳማት መንፈሳውያን አገልጋዮች ካህናት ራሳቸውን በራሳቸው ለመርዳት ሲጣጣሩ ከአልታየ በቀር ሌላ ተጨማሪ ርዳታ ለማግኘት እንደማይችሉ እሙን ነው ።

እግዚአብሔርም ቢሆን የሚረዳው ራሳቸውን መርዳት የሚችሉት ወጥተው ወርደው ከሆነ ራስን በራስ መርዳት የተፈጥሮ ግዴታና ዘወትር ከሚፈጸሙት ምግባር ትሩፋት ገብቶ የሚቀጠር መሆኑን መንፈሳውያን አገልጋዮች ሊገነዘቡት ይገባል ።

የሌላው ዓለም አብያተ ክርስቲያናት በየጊዜው የርዳታ እጃቸውን ሊዘረጉ የቻሉት በምእመናኖቻቸው አስተዋፅኦና በየገዳሞቻቸው እንደዕጣን ፡ ጧፍ እንደ ግህልና ዕዋዕ የመሳሰሉትን የልማት ሥራዎች በማቋቋም የአገልጋዮቻቸው ካህናት አዕምሮና ጉልበት ከአስገኘው በረከት እየከፈሉ እንጂ እንደመና ከሰማይ እየወረደላቸው አይደለም ።

በዚሁ አንፃር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት በአእምሮም ሆነ በጉልበት ከሌሎች የአነሱ ናቸውን? ተከታዮቻቸው ምእመናንስ በአስተዋፅኦ የደከሙ ናቸውን? ሁለቱም ወገኖች በማንኛውም የባሕር ማዶ አብያተ ክርስቲያናት አባላትን እጅ በመመልከት ብቻ መኖር አይገባቸውም ሁሉም ካህናት በልማት ሥራ በመሠማራት ራስን በራስ አልምቶ ለሌላው ጭምር መልካም አርአያና ምሳሌ መሆን ያስፈልጋል ።

ከላይ እንደጠቀስነው ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን የምትችለው የየአንዳንዱ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የካህናት መሠልጠኑ ጉዳይና ለየሰበካቸው ምእመናን በቅድሚያ ትምህርተ ወንጌል የመስጠቱ ኃላፊነት የሚመለከታቸው መሆኑን ተገንዝበው ትኩረት እንዲያደርጉበት መጣጣር ይኖርባቸዋል ።

በየጊዜው የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ካህናት የመንፈሳዊ አገልግሎት ተግባር ሥራ በየተራ በመሆኑ በዕረፍት ጊዜያቸው ጥያቸውን ያላሻሻሉ አንዳንድ ካህናት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ሌሎችም የተግባረ እድ (የልማት ሥራ) ተቋሞች እየተቋቋሙላቸው እንዲሠሩ በየጊዜው መመሪያ መስጠቱ ግልጽ ነው ። አንድ ገበሬ ዱሩን መንጥሮና አቃጥሎ ሳሩን አጭዶ ድንጊያውን ፈንቅሎ መሬቱን አርሶና አለስልሶ የተበጠረውንና የተንጠረጠረውን ዘሩን ከጐተራ አውጥቶ የሚበትነው ለከንቱ አይደለም መሬት የተቀበለችውን ዘር ጨምራ አብዝታ ትርፍርፍ አድርጋ መልሳ እንደምታበረክተው በመተማመን ነው ።

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናትም የመጀመሪያው ሰው ሠርቶ በወዙ እንዲጠቀም በታዘዘው መሠረት በተለይ በገጠሩ ኢትዮጵያ ያሉት ሁሉም በልማት ሥራ ተሠማርተው የሚገኙ በመሆናቸው ከልማቱ ሥራ ወደኋላ ያሉበት ዘመን አይገኝም ።

የልማት ሥራ እንደሌላው በየጊዜው በዘመናዊ አሠራር የሚካሔድ ከሆነ ጥቂት ዘርቶ ብዙ ማምረት ፡ በጥራት አቅርቦ ከፍ ያለ ዋጋ ማግኘት የሚቻለው በአዋቂዎች አመራር ሲከናወን እንደሆነ ሁላችንም ልናምንበት ያስፈልጋል ።

በአብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤቶች የልማት ሥራዎች እየተቋቋሙ በመገናኛ ዘዴዎች ዜናዎች እየተሰተጋባ ከቆየ በኋላ የውሃ ሽታ እየሆኑ የቀሩ እንዳሉም ስለምናውቅ አስቀድሞ በጥናት መቋቋም እንዳለባቸው ሳናስገነዝብ አናልፍም ።

አንዳንዶች በጥናት የተቋቋሙት እንደየካይብረ ግህል ቅ/ሚካኤል ዳቦ ቤትና እንደገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ አብያተ ክርስቲያናት ተግባረ እድ የልማት ሥራዎችና የመሳሰሉት ሁሉ በመልካም አርአያነታቸውና ምሳሌያቸው ተጠቅመን የተቋቋሙት እንዲጠናከሩ ያላቋቋሙት በጥናት ተደራጅተው አሁን ከአሉበት የኑሮ መሻሻል እንዲያሳዩ አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባኤ አባላት ከመንፈሳዊ አገልግሎት ጋር የልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ትኩረት እንዲሰጡበት ለማሳሰብ እንወዳለን ።

ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ወንድም

# እልክላችሁአለሁ

እልክላችሁአለሁ ፡ የሚለው ቃል ሰጪና ተቀባዩን በአንድነት አጣምሮ የያዘ ቃል ሲሆን ፡ መሠረቱም በኢትዮጵያችን "ፈነወ ላከ" ከሚለው ግዕዝ የተወሰደ ቃል ነው ። በሰጪና በተቀባይ መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ ። ይኸውም ሰጪው ካለው ፡ ከሞላውና ከተትረፈረፈው ቀንሶ በተቀባዩ ዘንድ አንድ ነገር ለማስገኘት የሚያደርገው ችሮታ ሲሆን ተቀባዩ ደግሞ ምንም ሳይኖረው የተሰጠውን ተቀበሎ ማመስገንና ሰጪውን ማወደስ የተለመደ ተግባር ነው ።

ለምሳሌ፡ ከአገር ውጪ የሚኖር ልጅ ወይንም አባት ፡ ሌላውም ሁሉ ለሚወደው ፡ ለሚያፈቅረውና ለሚሳሳለት ይሆናል ብሎ ያመነበትን ስጦታ ይልካል ፡ የተላከለትም ሰው በፖስታም ይሁን በእጅ ሲደርሰው በደስታ ተቀብሎ የተላከለትን ዕቃ በተግባር ላይ ያውለዋል ።

ታዲያ በላኪና በተቀባይ መካከል የሚኖረው መግባባትም በዚሁ ዓይነት የሚቀጥል ሲሆን ፡ ከተግባቡም በኋላ አስደናቂና ተአምራታዊ ተግባራት ያስገኙብ ይከናወናሉ ።

## የተልዕኮ ወይንም የመላክ ዓይነቱ ብዙ ነው

ለምሳሌ፡- አንድ ወታደር ሀገሩንና ዳር ድንበሩን እንዲጠብቅ ይላካል ፡ ሲላክም ሙሉ ትጥቅ

፲ ፲፩

www.ethiopianorthodox.org

ታጥቆ ፤ ስንቅ ይዞ ፤ መመሪያ ተሰጥቶት ስለሚላክ ድል መትቶ፤ በድል ተሞልቶ ፤ ሺህ ገዳይ ፤ እልፍ ገዳይ ቀዳሳሙ ፲፰-፲፯—፱ እየተባለ እየተዘመረለት ይመለሳል ፤ በደስታ ወጥቶ በድል ይገባል ። ሳሙኤቀዳማ ፲፯ ቁ ፩ ፍጻሜ ፤

በመሠረቱ ይህንን ለማለት ያስደፈረን በዮሐንስ ወንጌል ፲፬ ቁ ፲፭—፲፯ እና ፲፭ ቁ ፳፮ የተጠቀሰው ቃል ነው ፤ ቃሉም እንዲህ ይላል "ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል ፤ እኔ የምልክላችሁ መንፈስ ከአብ ዘንድ የወጣ የእውነት መንፈስ ነው" የሚል ነው ።

ይህ ቃል የተነገረው ለሐዋርያት ሲሆን ወቅቱም የዛሬ ፲፱፻፶፪ ዓመት ገደማ በኢየሩሳሌም ነው ፤ በዚያን ጊዜ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መቶ ሃያውን ቤተሰብ በአንድነት ሰብስቦ በኢየሩሳሌምና አካባቢዋ በሚያስተምርበት ጊዜ "እገረፋለሁ ፤ እሰቀላለሁ ፤ እሞታለሁ ፤ በ፫ኛውም ቀን እነሣለሁ እያለ ሲነግራቸው ያዝኑ ፤ ይተክዙ ፤ ተስፋም ይቆርጡ ስለነበር" በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዟችሁ ። እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ እወስዳችሁኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ስጦታ ደግሞ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም "ዮሐ ፲፬ ቁ ፲፰ ፳፭—፳፱ እያለ በሰፊው ከአጽናናቸው በኋላ እንግዲህ አሕዛብን ሁሉ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁአቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችሁአቸው ደቀመዛሙርት አድርጓአችው እኔ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር ነኝ ማቴ ፳፰ ቁ ፲፱—፳ በማለት ሲልካቸው የሚያስፈልጋቸውን ማለትም መያዝ የሚገባቸውንም መሣሪያ በዝርዝር አስረድቶአቸዋል" ወርቅ ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ ፤ ወይም ለመንገድ ከረጢት ፤ ወይም ሁለት እጅ ጠባብ ፤ ጫማ ፤ በትር አትያዙ—ማቴ ፲—፱ እና ፲ ብሎ ካስጠነቀቃቸው በኋላ በምትኩ "ሰላም ለእናንተ ይሁን አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችሁአለሁ ፤ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" ብሎ "እፍ" እንዳለባቸውና ሥልጣንን እንደሰጣቸው በዮሐ ፳—፳፩ እና ፳፪ ላይ ተዘግቦ ይገኛል ።

ታዲያ "መንፈስ ቅዱስን እልክላችሁአለሁ" ብሎ በገባላቸው ኪዳን መሠረት ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በ፵ኛው ወደ ሰማይ ባረገ ፲ኛው ቀን ሁሉም ተሰብስበው በአንድ ልብ በሚኖሩበት ቤት እያሉ አንድ ቀን ጧት ሳያስቡት በድንገት ዘላቂ የሆነው ትጥቃቸው ሲሰጣቸው ዐይኖቻቸው እያዩ ጆሮዋቻቸው እየሰሙ ነበር፤ በወቅቱም እንደአውሎ ነፋስ ያለ ከባድ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ በተቀመጡበት ቤት ሙሉት አለ ፤ የእሳት ነበልባሎችን በማየታቸው ተደናግጠው እንደቆሙ እነ ዚያ ነበልባላውያን ልሳናት በያንዳንዳቸው ራስ ላይ አረፉ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው በ፸፪ ቋንቋዎችም የእግዚአብሔርን ቃል እየተረጎሙ ከመላው ዓለም ለመጣው ሕዝብ በየቋንቋው አስረዱ አግልግሎታቸውን በስፋት ፤ በብዛትና በጥራት ጀመሩ ፤ ሁኔታውም ከዓለም ዳር እስከ ዓለም ዳር ተዳረሰ ። የሐሥ ፪—፩ ፍጻሜ ፤

እልክላችሁአለሁ ባላቸው መሠረት መንፈሱን ስለላከላቸው የሰውን ፊት አይተው ከመፍራት ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝና እሱን ማገልገል እንደሚበልጥባቸው በድፍረት ማስረዳት ቻሉ የሐሥ ፬—፲፱ እና ፳ ፤

ስለዚህ ይህንን ጽሑፍ ያነበብን ሁላችን እግዚአብሔር አምላካችን የሁሉ ጌታ ፤ ለሚለምኑት ሁሉ የማያልቅበት ባለጠጋ ፤ ስሙን የሚጠሩትን ሁሉ የሚያድን በመሆኑ ሮሜ ፲—፲፪ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠውን መንፈስ ቅዱስ ለእኛም እንዲሰጠንና እንደ ነርሱ የተሰጠንንና የተላክንበትን ተግባር በመልካም እንድናከናውን ይረዳን ዘንድ መልካም ፈቃዱ ይሁን አሜን ።

ቀሲስ ምሕረት ዘውዱ

# ጋብቻና…

(ከገጽ ፳፬ የዞረ)

ባሏ መሆኑን በትክክል ስለምትረዳ ሁልጊዜ ወደ ቤተሰቦቿ ትኮበልላች ቤተሰብእ አከላከሉና ተቆጥቶ ቢመልሳትም ቅራኔው እየበዛ የጋብቻ ፍቺ መፈጸም የኋላ ውጤት ሆኖ ቆይቷል ።

ይህ ዓይነቱ ጋብቻ በሁለተኛው ክፍል የተጠቃለለ ሆኖ ከነ ዚህ ወገኖች የሚወለዱትም የአባትና የእናት እንክብካቤ የተለያቸው በመሆኑ አደገኛ አዝማሚያን የሚከተሉ ቤተሰቦች ይሆናሉ።

ሌላው መጥፎ አዝማሚያ የሚገጥመውን የኅብረተሰብእ አካል ስንመለከት ይህ የሚገኘው ከጋብቻ ውጭ በሚወለዱት ክፍሎች ነው በዕለት ፍትወታዊ ስሜት ተገፋፍቶ ወይንም ዕለታዊ ችግርን ብቻ በዕለቱ ብቻ ለመቋቋም በሴት አዳሪነት ሕይወትን አቅርቦ ራስን ለርኩስ ህልውና በመለወጥ በሚያደርጉት ርካሽ የሆነ ሥውርና የደራ የአካል ገቢያ ባለው

(ወደ ገጽ ፫ ይዞራል)



# የየጭቃ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ባጭሩ

## ዘግይቶ የደረሰን ዜና

ይህች ደብር የምትገኘው በጎጃም ሀገረ ስብከት በሞጣ አውራጃ ክልል ሲሆን የተተከለችውም በአብርሃ ወአድብሐ ዘመነ መንግሥት ነው ።



የጭቃ ማርያም ቤተ ክርስቲያን

በዚህችም ጥንታዊት ደብር ከየሞያ ዘርፉ እያሌ የአብነት መምህራን የነበሩባትና አሁንም ያሉባት በመሆኑ ከነዚሁ የአብነት መምህራንም ተምረው በርካታ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ፈልቀውባታል ፤ አሁንም እየፈለቁባት ነው። ከነዚህም ሊቃውንት መካከል ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ይገኙበታል ።

ድውያንንም (ሕሙማንንም) በመፈወስ በኩል በዚህች ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ግቢ በሚገኘው ዐበል በመጠመቅ በየዕለቱ ብዙ ሕሙማን ከልዩ ልዩ በሽታዎች ተፈውሰዋል ። እየተፈወሱም ነው ። ይልቁንም በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥንትም ሆነ አሁን ከ፴ እስከ ፵ የሚደርሱ መናንያን መነኮሳት/ባሕታውያን ዘግተው ስለሚኖሩባት በይበልጥ ታሪኳ እንዲጉላ አድርገውታል ።

ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያኑ

# ዜና ሊቃውንት

## የአለቃ ኃይለ ኢየሱስ አፈሩ አጭር የሕይወት ታሪክ ፤

አለቃ ኃይለ ኢየሱስ ከአባታቸው ከአቶ አፈሩ ደግፍና ከእናታቸው ከወይዘሮ ወለተማርያም ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፲፰፻፸፮ ዓ/ም በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ በእንግሮ ወረዳ ልዩ ስም ደድኖ በሚባለው ቀበሌ ተወለዱ ።

እድሚያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚሁ ቤተ መቅደስ ከመሪጌታ ውቤ ዘንድ የንባብ ትምህርታቸውን በሚገባ ከፈጸሙ በኋላ ፤ ወደሌመን ሥላሴ ደብር ሄደው ከመምህር ወልደ ሚካኤል ጾመ ድጓና ምዕራፍ ከመማራቸውም በላይ የዲቁና መዓርግ ተቀብለው በዲቁና ተተክለው በቅዳሴ አገልግለዋል።

አለቃ ኃይለ ኢየሱስ ትምህርታቸውንና ዕውቀታቸውን ከፍ ለማድረግ ወደቤጌምድር ሄደው አዛውር ኪዳነ ምሕረት ከምትባለው ደብር ከታወቁት የቅኔ መምህር ከመምህር ጽጌ ቅኔን ተምረዋል ። ፍትሐ ነገሥትንም አሂደዋል የራስ ሚካኤል ጉልት ከነበረው ዳባት ቅዱስ ጊዮርጊስ (አራዶጃን) ከሚባለው ደብር ከመምህር ዘለለው ካሣ ዘንድ ድጓን በሚገባ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል። ከዚያም ትምህርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ በመቀጠል ወደደብረ ታቦር ሄደው ከመምህር ሠርፀ ድንግል ዘንድ የተክሌን ዝማሜ ከነባህሉ ተምረው



አለቃ ኃይለ ኢየሱስ እኒህ ነበሩ

በመምሕርነት ተመርቀዋል ። እንዲሁም ጎንደር ሄደው ከመሪጌታ ላቀው ዘንድ የጐንደርን የዐናዕል ባህልና ሥርዓት ተምረው የዚሁ ሞያ በመምህርነት ተመርቀዋል ። እንዲሁም ወደ ዙር አምባ ሄደው ከታላቁ መምሕር ከብካብ ዘንድ ዝማሬና መዋሥዕትን ተምረው በመምሕርነት ተመርቀዋል።

አለቃ ኃይለ ኢየሱስ አፈሩ ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ትምህርታቸውን በየደረጃውና በየክፍሉ በሚቀስሙበት ወቅት ቀደም ብለው የገበዩትን ትምህርት በደረ

ሕንፃ ረጅም ጊዜ ያለው ከመሆኑም በላይ ክዳኑም የሣር በመሆኑ ለዐሐይና ለዝናም ተጋልጦ ነበር ። ይህንንም ዓቢይ ችግር የአካባቢው ሕዝብ ተገንዝቦ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡንና ጉልበቱን አስተባብሮ ሕንፃውን ለማደስና የቆርቆሮ ክዳንም ለማልበስ ከፍተኛ መረባረብ ባደረገበት ወቅት አቶ አድምጤ ዐጋው የተባሉት በጎ አድራጊ ከግል ገንዘባቸው ብር ፮ሺህ፪፻፳ (ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ አውጥተው ቆርቆሮና ሌሎችንም አስፈላጊ ነገሮች አሟልተው በማቅረብ የሕንፃው ዕድሳት ከተጠናቀቀ በኋላ ግንቦት ፳፪ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም ተመርቆ ታቦቷ ከመቃኞ ቤት ወደ ጥንታዊ መንበር ገብታለች ።

መ/ዘሪሁን ታረቀኝ



www.ethiopianorthodox.org

ጀው ከማስቀጸልና ከማስተማር ፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከማገ ልገል ያልተቆጠቡ ቢሆኑም ፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ፡ ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም” ብሎ ያላወቁትን ፡ ያልተማሩትንና ያላመኑትን እን ዲያስተምሩ የአዘዘውን ትእዛዝ አብነት በማድረግ ፡ አለቃ ኃይለ ኢየሱስ አፈሩም ከቀለም ወላጆቻ ቸው ጸሎተ ቡራኬን ተቀብለው ወንበር ዘርግተው እንዲያስተምሩ ተፈቅዶላቸው ጉባዔ ዘርግተው ፡ አቋቋሙን ፡ ዝማሬ መዋሥዕቱን ፡ ሌሎችንም የቀለማት ድትበሃልና ልማድ ፡ በሥፊው አስተምረዋል። ይኸውም በጐንደር ሃያ ዓመት ፡ ካስተማሩ በኋላ ፡ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ በ፲፱፻፳፫ ዓ ም ወደ ሸዋ አስመጥተዋቸው በሰላሌ አውራጃ በፍቼ ገነተ ጊዮርጊስ ደብር እንዲያስተምሩ መድበዋቸው አስ ተምረዋል።

አለቃ ኃይለ ኢየሱስ አፈሩ የቀሰሙትንና የተማሩትን ሁሉ ያለምንም መሰልቸት ለራሳቸው የግል ሹመትና ድሎት ሳይሹ ተዚ ዘረው የሰበሰቡትን የዕውቀት ምርት ሁሉ ለቀረበላቸው ሰው በነፃ ስጦታ ሰጥተዋል ። በማስተ ማር ረገድ ከላይ እንደተገለጸው በጐንደር ሃያዓመት ፡ በሸዋ ፶ ዓመት በድምሩ ሰብዓ ዓመት በማ ስተማር ለቤተ ክርስቲያናችን በር ከት ያሉ መምህራንን አበርክተ ዋል ። እነዚያም ዛሬ በየተሠማሩ በት አገልግሎታቸውን እያበረ ከቱ ናቸው ።

## ሽልማት

አለቃ ኃይለ ኢየሱስ አፈሩ በ፲፱፻፳፱ ዓ/ም ከልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ካባና የሐር ቀሚስ ፡ ሱሪና እጀ ጠባብ ተሸልመዋል ። በ1930 ዓ/ም ከደጃዝማች ተክለ ማርቆስ እንደዚሁ ሙሉ ሽልማት ተሸልመዋል ። በ1934 ዓ/ም ርዕሰ ደብር ዘፍቼ ገነተ ጊዮርጊስ ተብ ለው በመሰየም ይህንን ታዋቂና ጥንታዊ ደብር ከመምራታቸውም በላይ ፡ ከእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፡ ኋላ ፓትርያርክ ባስልዮስ ሙሉ ሽልማት ተቀብለዋል ።

## ተክሊላዊ ጋብቻ ፡

አለቃ ኃይለ ኢየሱስ አፈሩ ለአባታቸው ለአዳም ፡ ለእናታ ቸው ለሔዋን በታዘዘው መሠረት በ፲፱፻፳፭ ዓ/ም ወይዘሮ ፋንታዬ ዘአማኑኤልን አግብተው ሁለት ልጆችን ወልደዋል እነርሱም አሁን በሕይወት ይገኛሉ ።

አለቃ ኃይለ ኢየሱስ ከማስተ ማር የሚተርፋቸውን ሰዓት የሚያ ሳልፉት በጸሎትና በስግደት ነበር።

ምንም ቢያውቁና ቢመራመሩ፡ ሞተ ሥጋን ያሸነፈ ሰው የለምና ይልቁንም የእግዚአብሔርን ስማ ያዊ ፀጋ ማግኘት የሚቻለው በሞት መሰላልነት ተሸጋግር ለት ንሣኤ ዘጉባዔ በቅቶ ሲገኝ ነውና እድሜንም እንደትምህርታቸው ሁሉ ጠግበው በተወለዱ በአንድ መቶ ስድስት ዓመታቸው በሞት ተለይተዋል ። ከአባቶቻቸው አምባ አንቀላፍተዋል ።

ከቤተሰቦቻቸው

# ዜና ሊቃውንት ወዜና ዕረፍት

## የመምህር ድሜጥሮስ አጭር የሕይወት ታሪክ

መምህር ድሜጥሮስ ስመኝ ከአ ባታቸው ከ... ስመኝ መለሰ ከእ ናታቸው ከወይዘሮ ደስታ ትርፌ በጐጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ማር ቆስ አውራጃ በድላንታ ማርያም በ፲፱፻፵፬ ዓ ም ተወለዱ በዚህም መሠረት እድሜአቸው ለትምህ ርት እንደደረሰ የደዋራች ቅ ጊዮር ጊስ አተባለው ቀበሌ ከመሪጌታ ገብረ ሥላሴ ንባብና ዳዊት በሚ ገባ ተምረዋል ። ከዚያም በኋላ በልዩ ልዩ ቦታ እየተዘዋወሩ ሲማሩ ቆይተው በብቸና አውራጃ በምትገኘው ማርቆርቆሪያ ማር ያም ሄደው ከመምህር አባ ይትባ ረክ ጾመ ድጓና ቅኔ በሚገባ ተምረ ዋል ። ከዚያም በኋላ ከታላቁ ገዳም ዲማ ቅ.ጊዮርጊስ ከአለቃ ማርቆስ ብሉይና ሐዲስ በሚገባ ተምረዋል ። መምህር ድሜጥሮስ ይህን ሁሉ እንደጨረሱ በዚህ ዓለም ሳይወሰኑ እዚያው እገዳሙ ሱባዔ ገብተው ፲፯ ዓመት ዘግተ



መምህር ዲሜጥሮስ እኒህ ነበሩ

ዋል መምህር ድሜጥሮስ ከአሉ በት ቦታ ቅሉ ሕዝብን ማስተዳ ደር ቀላል ሥራ ባይሆንም ከለፈ.ቃ ዳቸው እያለቀሱ ወጥተው ለታ ላቁ ገዳም ለዲማ ቅ.ጊዮርጊስ መምህር ሆነው ሲያስተዳድሩ ... ሥራ ልማታቸው ።

፩ኛ/ የወንድ ገዳም ፲፬ ክፍል ቤት ቆርቆሮ

፪ኛ/ የእንግዳ መቀበያ ፭ ክፍል ቆርቆሮ በአስፋልት የተሠራ

፫ኛ/ የሴት ገዳም ፬ መቶ ቆር ቆሮ ፪ ሳጥን ምስማር ገና ያልተ ሠራ

፬ኛ/ ፩ ወፍጮ

፭ኛ/ ፭ ጥማድ በሬ

፮ኛ/ ለታቦቱ የመብራት ኃይል

፯ኛ/ በእርዳታ የነበሩ ፫ መቶ ደካሞች ከመንግሥት የሚረዱ ይህንን ሁሉ ሥራ እየሠሩ ፲፭ ዓመት ካስተዳደሩ በኋላ የሥራ እድገት በማግኘት አዲስ አበባ ውስጥ ሰዋስወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት ፫ ዓመት ከ፲ ወር ካስተማሩ በኋላ በደረሰባቸው ሕመም ,ሐምሌ ፩ ቀን ፹፩ ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

መካነ መቃብራቸውም ደብረ ሊባኖስ ሆኗል ።

ከዚህ ቀጥለን የኀዘን እንጉር ጉሮ እናቀርባለን ።

## የኀዘን እንጉርጉሮ

ዘመድ ልትረዳ እንዲሁም ልታስ
ተምር ነበር ደረጃህ
ደመና ሳይዳምን በረዶ መታህ
ዳዊትክን መጽሐፉን ማን ተቀበ
ለው
እንደ አንተ እንብቦ ላይተረጉ
መው
ሞት አደጋ መታው ሆነ እንዳልተ
ማረ
እፈልገው ነበር የእናቱ ልጅ እንቱ
እስኪ ጠይቁልኝ ከቤተ ክህነቱ
ዳዊት ወዳጁ ነው ጸሎት ወዳጁ
ነው አይጠፋም ከቤቱ
ዕውቀትህ ሊቀዳ ተዘጋጅቶ ነበር
አሁን ምን ቸገረው ትምህርት
ዕውቀትህ አብሮ ባይቀበር
ዕውቀትክን ይወቀው ሁሉም ኃዘ
ንተኛ
መምህር ድሜጥሮስ እጥፍ ብለህ
ተኛ
ምን አሳዘኝ ሰው ነኝ ጠያቂ
ማጣቴ
እኔ ወደኋላ አንተ ወደፊቴ
መምህር ያንተ ሹመት ምን ጊዜ
ተፈታ
ለካስ እንዲህ ነው ወይ በረዶ
ሲመታ
በሚያዘው ሥራ መምህር ድሜጥ
ሮስ የሚዋብበት
ደብት ተቀበረ ያን ያህል ዕውቀት

እኅታቸው ወይዘሮ
ጥሩወርቅ ስመኝ

# ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ

ቅዱስ ያሬድ የተነሣው በ፮ኛው ምእት ዓመት መጀመ ሪያ፡ በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው ትውልዱም በት ግራይ ሀገረ ስብከት በአኩስም ሲሆን አባቱ ዮስጦስ እናቱ ታው ክልያ ይባላሉ (አባቱ አብርሃም እናቱ እቅሌስያ የሚሉም አሉ) እድሜው ለትምህርት ሲደርስ የአ ኩስም ጽዮን ገበዝ ወደነበረው ጌዴዎን ወደሚባለው አጎቱ ዘንድ ሄዶ ትምህርት ጀመረ ።

ቅዱስ ያሬድ በትምህርት ቤት ሳለ በግብረ ገብነቱና በትኅትናው የተወደደ እንደነበር ይተረካል ። ነገር ግን ትምህርቱ አልገባህ ብሎት ለብዙ ዓመታት ያህል ደከመ ስለዚህም ከዕለታት አንድ ቀን መምህሩ ተቆጥቶ ቢመታው ፩ኛ ትምህርቱ አልገባው በማ ለቱ፡ በመምህሩ ቁጣ ተበሳጭቶ ትምህርቱን ትቶ ወደበረሐ ሲኰዝ ደከሞት በአንዲት ዛፍ ሥር እንዳ ረፈ አንድ ምሳሌ ያያል ።

ይኸውም አንዲትትል ወደዛፉ ላይ ለመውጣት እየተንጠለጠለች ስትወድቅ ፡ ስትነሣ ለብዙ ጊዜ ከቆየች በኋላ በመጨረሻ ወደዛፉ ቅርንጫፍ ላይ ለመድረስ ስትበቃ በማየቱ “እኔም እስከመጨረሻው ልሞክር” በማለት ተስፋ ሳይቆ ርጥ እንደገና ወደመምህሩ ተመ ልሶ ይቅርታ ጠየቀ መምህሩም ይቅርታ አድርጎለት ፡ ወደ እግዚአ ብሔር ከጸለየ በኋላ ትምህርቱን ጀምሯል ።

ከዚህ በኋላ አእምሮው ተከፍቶ ለት የብሉያትንና የሐዲሳትን (፹፩) መጻሕፍት በአንድ ጊዜ ፈጽሞአል ። እግዚአብሔር “እነሆ መንፈሴን አፈስስላችኋ ለሁ ቃሌንም አስተምራችኋለሁ” (ምሳሌ ፩፡፳፫) ባለው መሠረት መታሰቢያውን በእርሱ ሊያቆም ወድዷልና ከዚሁ በመቀጠል ፡ ወደቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሃሌ ሉያ ለአብ ፡ ሃሌ ሉያ ለወልድ ፡ ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ ቀዳ ሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ” በማ ለት በሦስት ሰዓት የሠለስት ዜማን ጀምሮ በየሰዓቱና በየቀኑ የሚጸለይ የዜማ ድርሰቱን ቀጥ ሏል ።

የቅኔቱ ካህናተ ሰማይ ዝማሬ ተገልጾለት በግዕዝ ፡ በእዝል ፡ በአራራይ እያፈራረቀ እግዚአብ ሔርን አመስግኗል ። የዜማዎቹም ክፍሎች ዋና ዋናዎቹ እነዚህ ሦስቱ ይሁኑ እንጂ ለእያንዳንዳ ቸው የተለያዩ ቤቶችና ስልቶች አሏቸው ። በዓለም ላይ ያሉ ዜማ ዎች ፡ ዘፈኖችና ሙዚቃዎች ሁሉ ከነዚህ የዜማ አይነቶች ውጭ እንዳልሆኑ በቃናቸውም ሆነ በዜማ ሊቃውንት የተረጋገጠ ነው ። ሰዎች ለምስጋና ፡ ለሐዘን ለደስታ፡ በተለያዩ መግለጫዎች ስሜታቸውን የሚገልጹበት እንጉ ርጉር ሁሉ በቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ የተመሠረተ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ያሬድ ይህን መንፈሳዊ ዜማውን የደረሰው ከብሉያትና ከሐዲሳት ፡ ከሊቃውንትና ከእራሱም ድርሰቶች ሲሆን ንባቦቹ ዘመኑንና በዓሉን የሚመለከቱ ፡ የረቀቀ ምሥጢር ያላቸው ናቸው። የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ፡ ልደቱን ፡ ጥምቀቱን ፡ ሞቱን ፡ ትንሣኤውን ፡ ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱን ያብራራሉ ።

እንዲሁም በአራቱ ወቅቶች በክረምት በሐጋይ ፡ በመፀው በጸደይ በመክፋፈል የወራቶችን ጠባይ በመግለጽና የእመቤታችን የድንግል ማርያምንና የተለያዩ ቅዱሳንን ክብረ በዓላት እያስፋፋ ድጓውን ደርሷል ። የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ዜማው ብቻ ሳይሆን የንባቡም ምሥጢር ልብ ይማርካል ። ከዚህም የተነሣ በዓፄ ገብረ መስቀል ፊት ቆሞ ንባቡን ከዜማው እያስማማ ሲዘምር ሁለቱም በመንፈስ ተመስጠው ያሬድ በመቋሚያው የንጉሡን እግር ቢወጋው ፈጽሞ አልተሰማውም "ልቡ መልካም ነገርን አፈለቀ ። እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እናገራለሁ" (መዝ.፵፬ ÷ ፩ ።

ቅዱስ ያሬድ ይህን በዓለም ላይ የተደነቀ ፡ የቤተ ክርስቲያን ዐይን የሆነ ዜማውን በሚደርስበትና በሚያዜምበት ጊዜ በዘመኑ የነበረው ንጉሥ ሠራዊቱና ሕዝቡም ወደእርሱ እየቀረቡ በማዳመጥ ያደንቁ እንደነበር ኋላም መንኩሶ በምናኔ ሲለያቸው እንዳዘኑ በስንክሳሩ ተጽፏል ። ዛሬም ለቤተ ክርስቲያናችን ያበረከተውን መንፈሳዊ ቅርስና ፡ ለዓለም ሙዚቀኞች ያስተላለፈውን ስልተ ዜማ ስንመለከት ይህን ታላቅ ውለታውን እንደቀላል ነገር ሳንቆጥር ማሰብ ይገባናል ።

ይህ ኢትዮጵያዊ ድርሰቱንና አገልግሎቱን በአክሱም ጽዮን ከፈጸመ በኋላ ወደሰሜን ሄዶ ጸለምት በተባለው በረሐ ገብቶ በጾም በጸሎት ተወስኖ ፈጣሪውን እየመሰገነ ከኖረ በኋላ ግንቦት ፲፩ ቀን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተቀብሎ ተሠውሯል ።

ቅዱስ ያሬድ በራሱ ጥረትና ድካም አሳቡ እንዳልተሳካለት ስንመለከት ከሰውም ሆነ ከመንፈስ የምናገኘው ዕውቀት ሁሉ በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እንጂ በእኛ ጥረት ብቻ አለመሆኑን ከዚህ ታሪክ እንማራለን "እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም አልተማርሁትም" (ገላ.፩—፲፪) ሲል ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ቃል በእርሱም ተገልጾአል ።

ስለዚህ እንደሌሎቹ ቅዱሳን በሀገራችን ጽላት ተቀርጾለት ፡ ቤተ ክርስቲያን ታንጾለት ስለሚገኝ በተሰጠውም ቃል ኪዳን መሠረት አማላጅነቱን ተረድተን ከቅዱስ ያሬድ በረከት እንዲያካፍለን ስሙን በመጥራት መታሰቢያውን በማድረግ ክርስቲያኖች ሁሉ በዓሉን በደስታ ማክበር ይገባናል ።

መ/መንክር ዋሴ

## የሴቶች ዓምድ

# ከሰንበት ት/ቤት ምን እንማራለን ?

ከሰንበት ት/ቤት ለመማር ፡ መጀመሪያ ማጠናከር እንደሚታወቀው የሰንበት ት/ቤት በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን መቋቋም እንደሚገባው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ሕግና መመሪያ የሆነው ቃለዓዋዲ ያስተምረናል ።

በዚሁ የቃለ ዓዋዲ ደንብ መሠረት የሰበካ ጉባኤ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ በየደረጃው ሲቋቋም የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተጠናክሮ ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለ፳ት ጊዜያት ስብሰባ ሲያካሒድ ስለሰንበት ት ቤት መጠናከር ያልወሰነበትና ውሳኔ ያልሰጠበት ጊዜ የለም ።

የዚሁ የወጣቶች ጉዳይ መምሪያም እስከዚህም እርኪ ነው ባይባ



ሕፃን ራሔል ይህች ናት

ልም በየወቅቱ በሚያደርገው ሲሚናራዊ ስምሪት ለሰንበት ት ቤት መጠናከር የሚደረገውን አስተዋጽኦ ያመለክተናል ።



ሕፃን ማኅሌት

በተለይ ርእሰ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሆኑ አባቶች የቤተ ክርስቲያን ተተኪ የሚሆኑ ወጣቶችን ማፍራት ተገቢ መሆኑን የሚያምኑ በመሆናቸው በየአመራር ዘመናቸው የቃለ ዓዋዲው ደንብና የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ውሳኔ ተደምሮ በሥራ እንዲተረጎም የተጠናከረ መመሪያ ሰጥተዋል። አሁንም እየተሰጠ በመሆኑ ለሰንበት ት/ቤት ጥንካሬ መሠረት ሆኖታል ።

የየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤም ለሰንበት ት/ቤት የነበረው አመለካከት እስከዚህም የጐላ አልነበረም ፡ አሁን ግን ለሰንበት ት/ቤት የሚሰጠው ድጋፍና እንክብካቤ አጥጋቢና ተማሮችን የሚያሰባስብ ሆኖአል ።

ወጣቶችም ከዚህና ይህን ከመሳሰለው መመሪያና ድጋፍ በመነሳት ዛሬ በየሰንበት ት/ቤቱ የሚታዩ የወጣቶች ቁጥር እጅግ በጣም ከፍ እያለ በመታየቱ ያስደስተናል ። በተለይም የቃለ ዓዋዲው ፈጣሪ ለሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ድርብ ደስታ እንደሚሰማው አይጠረጠርም ።

በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የምፈልገው ግን ፡ በሰሜን ወሎ ሀ/ስብከት በቃሉ አውራጃ በከምቦልቻ ከተማ በሚገኘው በደብረ ፈራን ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ስለተቋቋመው የሰንበት ት/ቤት የትምህርት ይዞታ ጉዳይ ነው ።

ይህ ት/ቤት ነባር ወጣቶችና ወላጆችን በአንድነት አሰባስቦ እንዲሁም ሕፃናትን በሁለተኛ ደረጃ መድቦ እጅግ በጣም በተጠናከረ ሁኔታ በማስተማር ላይ ሲገኝ የወጣቶች ቁጥር በየጊዜው በእጥፍ እየጨመረ በማየታችን በተለይም እግዚአብሔር ኃይል መሆኑን የተረዳው ትውልድ ከሥራ ገበታው አንዱ በዕለተ ሰንበት የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና እግዚአብሔርን ማገልግል እንዲሆን ወስኖ የትምህርቱ ተሳታፊ ሆኖአል ።

በት/ቤቱ በመጠኑ ይህንን ከጠቀስኩ በኋላ በዚሁ ት/ቤት ከሚማሩ ሕፃናት መካከል ልዩ ተሰጥዎ የመንፈስ ስሜት ካደረባቸው ሁለት ሕፃናትን ለማስተዋወቅ ፈልጌአለሁ ።

ሕፃናቱ ማኅሌት ሙላት ዕድሜ ፬ ዓመት ከ፰ ወር

ራሔል አወቀ ዕድሜ ፬ ዓመት ብቻ ሲሆኑ በት/ቤቱ ውስጥ ያላቸው ስሜትና ተሳትፎ በጣም ተወዳጅነትን አትርፈዋል ።

ማኅሌት ሙላት ወደዚህ ት/ቤት ገብታ መሳተፍ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ የፕሮግራም ጊዜዋን ማክበርዋ በመዝሙር ዝማሬዋ በመድረክ ላይ ቁማ የመነጋገር ተሰጥኦዋ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ ለመልስ ተዘጋጅቶ መገኘትዋ ከዚህም ሁሉ በላይ ወላጆችዋ የዚህ ፕሮግራም ተሳታፊዎች እንዲሆኑላት የምታደርገው ጥረት በአጠቃላይ በትምህርት ቤቱ ሁለቱም ሕፃናት ኮከብ ሆነው በመገኘታቸው ያስደስታሉ።

ራሔል አወቀ በዚህ ት/ቤት ያላት ተሳትፎ ምሥጢረ ሥላሴን በማጥናት በጥያቄና የመልስ ወቅት በመጠየቅም ሆነ በመመለስ ያላት ስሜት ልዩ ሆኖ መታየታቸው በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ ካላት ልዩ ጠባይ ጋር የሚሰጠውን ትምህርት አትኩሮ በመቀበልና ለሚቀርብላት ጥያቄ አጥጋቢ መልስ በመስጠት እንደነባር ተማሪ የምትታይ ሆናለች ።

ቅ/ጳውሎስ የፀጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው እንዳለው በት/ቤቱ ብዙ ሕፃናት አሉ ፡ ነገር ግን የሁሉም ተሰጦ የተለየ ነው ።

ስለዚህም እነዚህ ሕፃናት በዚህ ሙርቃ እድሜአቸው በዚህ ዓይነት ተገንብተው በማየቴ የቤተ ክርስቲያናችን ልሳናት በሆኑ ጋዜጦችና መጽሔቶች ታትሞ ቢወጣ ለሰንበት ት ቤት መጠናከር አንደኛው መግሪያ መሆኑን ስላመንኩ ልኬዋለሁ ።

በአጠቃላይ በደብረ ፋራን ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ፡ ወላጆችና ሕፃናት በዚህ ዓይነት እየተሰባሰቡ አምላካቸውን በምስጋና እያገለገሉ በመሆናቸው የሚያስደስት ነው ። በዚሁ እንዲቀጥል እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሰላምን ያመጣላት ዘንድ ጸልዩ ።

በመጨረሻ የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ አጠቃልላለሁ "እንግዲህ ሰዎች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራሔ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው "ሮሜ ፲፪. ቁ. ፩—፫ ።

አስቴር ድንቁ

# ዜና ዕረፍት ዘሊቀ ካህናት ፀጋው ካሣ

## ዘግይቶ የደረሰን ዜና

ሊቀ ካህናት ፀጋው ከአባታቸው ከአቶ ካሣ ትኩ ከእናታቸው ከወ/ሮ ጥሩነሽ ሐብሉ በ፲፰፻፹፯ ዓ/ም ጥር ፲፮ ቀን በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ መካነ ኢየሱስ በተባለው ታላቅ ደብር ተወለዱ ።





www.ethiopianorthodox.org

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አባ ወልደ ማርያም ከተባሉት የንባብ መምህር ከፊደል እስከ ዳዊትና ሰዓታት ዲቁና ተማሩ ። በ፲፱፻፴ ዓ/ም ከአቡነ ማቴዎስ መዓርገ ዲቁና ተቀበሉ ።

ቀጥሎም በዚያው በተወለዱበት ደብር በዲቁና እያገለገሉ መሪጌታ ፈታሒ ከተባሉት የድጓ መምህር ጾዋትወ ዜማ በሚገባ ተማሩ።።

በ፲፱፻፲ ዓ/ም ከወ/ሮ ገሠሡች አበጋዝ ጋር በተክሊልና በቁርባን ሕጋዊ ሥርዓተ ጋብቻ ፈጸሙ ። በ፲፱፻፴፫ ዓ/ም ከአቡነ ይስሐቅ መዓርገ ቅስና ተቀበሉ ።

ሊቀ ካህናት ፀጋው መዓርገ ዲቁና ከተቀበሉበት ከ፲፱፻፴ ዓ/ም ጀምሮ ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ጽሙድ እንደ በሬ ቅኑት እንደ ገበሬ ሁነው አገልግለዋል ። ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎትም ጋር ቤታቸውንና በቤታቸው የሚኖሩትን ለመርዳት የሚጥሩበት የእርሻና የንግድ ሥራ እጅግ የሠመረ በመሆኑ ከራሳቸውና ከቤተሰባቸው አልፎ ሌላውን ለመርዳት ያስቻላቸው ስለነበር ድሆችንና አበያተ ክርስቲያናትን ሲረዱ ኑረዋል።

በዚህም መሠረት ሊቀ ካህናት ፀጋው ካሳ ፥

፩ኛ/ ተወልደው ለአደጉበትና ከዲቁና እስከ ቅስና ለአገለገሉበት ደብር ለመካነ ኢየሱስ ፥ ራዕየ ዮሐንስንና ገድለ መርቆሬዎስን በአንድ ላይ በብራና አስጽፈው ሰጥተዋል ።

፪ኛ/ በየጊዜው ጧፍ ዕጣን ሻማና ዘቢብ በገንዘባቸው እየገዙ በመስጠት ሲያገለግሉና ሲያስገለግሉ ኑረዋል ። እንዲሁም ለድኁን ማስፈያ ፶ ብር ረድተዋል ።

፫ኛ/ ለወቅጭት መድኃኔ ዓለም አንድ ድረሳነ ማኅየዊ መጽሐፍ በብራና ።

፬ኛ/ ለአምጃየ አቦ አንድ ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በወረቀት አስጽፈው ሰጥተዋል ።

፭ኛ/ ለዛናጨፈና ቅዱስ ጊዮርጊስ ወርቀ ዘቦ መጐናፀፊያና ቀሚስ

፮ኛ/ ለነፋሶ ቅዱስ ሚካኤል ሁለት ወርቀ ዘቦ መጐናፀፊያና አንድ መጋረጃና ሥዕለ አድኅኖ ከማበርከታቸውም ሌላ በየጊዜው ጧፍ ዕጣንና ዘቢብ ከማቅረብ የተቆጠቡበት ጊዜ አልነበረም ።

፯ኛ/ የሊቀ ካህናት ፀጋውን ደግነት ይበልጥ የሚያጐላው ደግሞ ከልጅነት ጀምሮ በግብርናውም ሆነ በንግድ ሥራ ከሳቸው ጋር ለረጅም ጊዜ ያገለገሏቸውን መንግሥቱ ጥሩነህ የተባለውን ሠራተኛቸውን ከልጆቻቸው በፊት ከራሳቸው ገንዘብ ወጭ አድርገው በከፍተኛ የሠርግ ድግስ ከመዳራቸውም በላይ ባላቸው የሥራ ልምድ መመሪያና ምክር እየሰጡት የሳቸውን ፈለግ ተከትሎ እንዲሠራ ማድረጋቸው ነው ።

ሊቀ ካህናት ፀጋው የሊቀ ካህናትነቱን መዓርግ የተቀበሉት የመካነ ኢየሱስን ፥ ቤተ ክርስቲያን ግብዝና ይዘው ያገለገሉ በነበሩበት ወቅት ነው ። በደብሩ ሥርዓት የገበዙ የመዓርግ ስም ሊቀ ካህናት” ነውና ።

ሊቀ ካህናት ፀጋው ከዚህ በላይ በተገለፀው መሠረት ቤተ ክርስቲያንን በማገልገልና ቤተሰቦቻቸውንም በመርዳት ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፵፯ ዓ/ም ባለቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ በ፲፱፻፵፯ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም ሥርዓተ ምንኩስና ፈጸሙ ። ከ፲፱፻፵፯ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፸፮ ዓ/ም በአዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል በቅስና ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ/ም ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ መካነ ኢየሱስ ተመለሱ። ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፸፮ ዓ/ም በተወለዱ በ፹፱ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።

ለብዙ ጊዜ ሲያገለግሉ በኖሩበት በመካነ ኢየሱስ ደብር ልጆቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው ተፈጸመ ።

ሊቀ ካህናት ፀጋው በየዓመቱ የካቲት ፲፮ ቀን የሚከበረውን የእመቤታችን የምሕረት ቃል ኪዳን በዓል በከፍተኛ ደረጃ ይጋብዙ የተራቡትንና የተጠሙትን ችግረኞች ያበሉና ያጠጡ ነበር ። ሊቀ



ሊቀ ካህናት ፀጋው እኒህ ነበሩ

ካህናት ፀጋው ፰ ወንዶች ፫ ሴቶች ልጆችን ወልደው እነዚህንም ሁሉ በሥርዓት አሳድገው ለወግ ለማዓረግ አብቅተዋል ።' በአሁኑ ጊዜ አንዱ ወንድና ሁለት ሴቶች ልጆች ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆኑ የቀሩት በሕይወተ ሥጋ በትዳር ላይ ይገኛሉ ። ሊቀ ካህናት ፀጋው ከ፰ በላይ የልጅ ልጆችን ያፈሩ ሲሆኑ አብዛኞቹም በቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተዋል ።

ሞት ለሥጋ ለባሽ ሁሉ የተወሰነ ስለሆነ እንደ ሊቀ ካህናት ፀጋው ካሣ በሕግ ተወስኖ ባለው ዕውቀት በተሰጠው ሀብተ ጸጋ እግዚአብሔርን በማገልገል ከአምላክ የተፈቀደለትን ዘመን ማሳለፍ መታደል ነው ።

ከቤተሰቦቻቸው



# ወርኃ ክረምት

በዓመት አራት ወቅቶች አሉ ። እነርሱም መጸው ፥ ፀደይ ፥ ሐጋይ፥ ክረምት ይባላሉ ። ወርኃ ክረምት ከሰኔ ፳፩ ቀን እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ያለው ነው ። በዚሁ ወቅት ምድር በጠለ ዝናም ትረካለች ፥ ማር ፥ ዕፅዋት ፥ አዝርዕትና አትክልት በቅለው የሚያድጉበት፥ ልምላሜ የሚያሳዩበት ፥ ምድር አረንጓዴ ለብሳ ፥ በስነ ጽጌያት የምታሸበርቅበት ወቅት ነው ።

ክረምት በሌሎች አገሮች በተለያዩ ወራቶች ይውላል። ለምሳሌ በእስራኤል አገር ዝናም የሚዘንመው ከጥቅምት እስከ ግንቦት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ። ይኸውም ፩ኛው በጥቅምትና በኅዳር የሚዘንመው ነው ። ሁለተኛው ወርኃ ዝናም ደግሞ በመጋቢትና በሚያዝያ የሚዘንመው ነው ።

ነቢዩ ኤርምያስ ይህንኑ በማስመልከት በመጽሐፈ ትንቢቱ እንደሚከተለው ጽፎአል “በልባቸው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናም በጊዜው የሚሰጠውን ለመከርም የተመደቡትን ወራት የሚጠብቅልንን አምላካችንን እግዚአብሔርን እንፍራ አላሉም” በማለት አመጸኞችን ከመዝለፉም በላይ በእስራኤል ምድር በዓመት ሁለት ጊዜ ዝናም እንደሚዘንም ያመለክታል ። (ኤር ፭ ፥ ፳፬)

እንዲሁም ሐዋርያው ያዕቆብ ይህንኑ መሠረታዊ ሀሳብ ደግፎ ከእምነት ጋር አነጻጽሮ ምሳሌያዊ ትምህርት ሰጥቶአል ። ይኸውም ገበሬ በትዕግሥቱ የምድሩን ፍሬ ለማግኘት እንደሚችል ሁሉ ክርስቲያኖችም ። እምነታቸውን አጽንተው በመያዝ የክርስቶስን መምጣት በትዕግሥት ከጠበቁ የማያልፈውንና የዘለዓለሙን ሕይወት የሚያሰጠውን ርስተ መንግሥት ስማያትን ለመውረስ እንደሚችሉ ሲያስገነዝብ “እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ ፥ እነሆ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናም እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል።” ይላል ። (ያዕ ፭ ፥ ፯)

ክረምት ማለት ወርኃ ዝናም ማለት ነው ፥ ሆኖም ዝናሙን እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲወድ ዝናመ ምህረት ያደርገዋል ። ሕዝቡን ሲጠላውና ሲቆጣው ደግሞ ዝናመ ምህረቱን ያቆማል ወይም ዝናመ መዓት ያደርገዋል ፥ ይህም ማለት ሰውም ፥ እንስሳውም ፥ ቤቱም አትክልቱም ፥ ዕፅዋቱም አዝርዕቱም ፥ ድንጋዩም አፈሩም የሚያጠፋና ጠራርጎ የሚወስድ ዝናም ያወርዳል ማለት ነው ፥ በዚሁ መሠረታዊ ሀሳብ ነቢዩ እግዚአብሔር ሙሴ ለሕዝበ እስራኤል የመሰነባበቻ ንግግር ሲያደርግላቸው በሚከተለው ኃይለ ቃል ነበር ። “የአምላክህን ትእዛዝ ብትጠብቅ ፥ በመንገዱም ብትሄድ እግዚአብሔር እንደማለልህ ለእርሱ የተቀደሰ ሕዝብ አድርጎ ያቆምሃል ። ሕዝቡም ሁሉ የእግዚአብሔር ስም በአንተ ላይ እንደተጠራ አይተው ይፈሩሃል ። እግዚአብሔርም እርስዋን ይሰጥህ ዘንድ ለአባቶችህ በመሰላቸው በምድርህ ላይ በሆድህ ፍሬ እግዚአብሔር በጎነቱን በላይህ ያበዛል። እግዚአብሔር ለምድርህ በወራቱ ዝናም ይሰጥ ዘንድ የእጅህንም ሥራ ሁሉ ይባርክ ዘንድ መልካሙን መዝገብ ሰማዩን ይከፍትልሃል ። ለብዙ አሕዛብም ታበድራለህ አንተ ግን ከማንም አትበደርም” ብሎአቸዋል ። (ዘዳ ፳፰ ፥ ፱ ፥ ፲፪)

በሀገራችንም ቢሆን ሁለት ዓይነት ወርኃ ዝናም እንዳለ እንገነዘባለን ይኸውም ከጥር ወር ጀምሮ የሚዘንመው የበልግ ዝናም እየተባለ የሚጠራው ነው ። በልግ የስጠ እንደሆነ ዓመቱን ሙሉ ጥጋብ ይሆናል ። በልግ ከሌለ ግን ዘመኑ አጻባ ነው ይባላል ። ገበሬውም ልፋትና ድካም ብቻ ሆኖ ይቀራል ።

በመሠረቱ ገበሬ ከዓመት እስከ ዓመት ከድካምና ከልፋት በቀር ዕረፍት የለውም ። ይኸውም በበጋ ጊዜ በመሬቱ ላይ ያለውን እሾህና ቁጥቋጦ ይጠርጋል ፥ ይመነጥራል ። በአንድ ቦታ ሰብስቦ በእሳት ያቃጥላል ። ማሳውን ያርሳል ያለስልሳል ለወርኃ ዘርእ ያዘጋጃል ወርኃ ዘርእ እንዳያልፍበትም በንቃት ይጠብቃል ። እንደ አፈሩ ወይም እንደ መሬቱ ዓይነትና መጠን ዘሩን ይመጣል ። ሞፎሩን ቀምበሩን ማረሻው ድግሩንና ዕርፉ ፥ ወገሉን ፥ ድግር ቅትርቱን ያደራጃል በሬዎቹን



www.ethiopianorthodox.org

ይንከባከባል ያዳብራል ።

ስለሆነም በሮቹ በእርሻቸው ወቅት በጉልበት ይስባሉ ፤ ያገለግላሉ ፤ ገበሬውም በደስታ በርካታ ያርሳል ያዘምራል ፤ ገበሬ ዘሩን የያዘ ስልቻ ፈትቶ በመዝሪያው ዕቃ ገልብጦ ከትከሻው ላይ ተሸክሞ ይንበረከክና "ጌታ ሆይ አንተን አምኜ እህሉን ከአፈር ጋር እቀላቅለዋለሁ (እደባልቀዋለሁ)። ስለዚህ ከቡቃያ ወደ ልምላሜ ከጽጌ ወደ ፍሬ አድርሰህ ከምድር አራዊት ከሰማይ አእዋፍ አካፍለህ አብላኝ" ብሎ በእምነት ከጸለየ በኋላ ይዘራል ።

ስለሆነም እግዚአብሔርም ንጹሕ ዝናሙን ያዘንማል ። መከሩም (እህሉም) ከከረጭ ከእንክርዳድና ከግንጭ የጸዳ ሆኖ ይገኛል ፤ በበረከትም ወደ ጎተራው ይገባል። ይኸውም ንጹሕ ዘር (መከር) በእውነተኞች አማንያን ከረጭ እንክርዳድና ግንጭ ደግሞ በዓመጸኞችና በእኩያን (በኃጥአን) ይመስላል" (ማቴ ፲፫ ፡ ፩ — ፴ ክረምት በዕለተ ምጽአት ይመስላል ። ክረምት አስፈሪ አስደንጋጭም ነው ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኢይኩን ጉያክሙ በክረምት ወበሰንበት" ማለት ሽሽታችሁ በክረምትና በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ ሲል ስለ ክረምት ክባድነትና አስፈሪነት በቅዱስ ወንጌሉ ገልጾልናል (ማቴ ፳፬ ፡ ፳)

ስለገበሬውና ስለግብርናውም ምሳሌያዊ ትምህርት አለው ። ይኸውም ገበሬው በትጉህ ሰባኬ ወንጌል ይመስላል ፤ የግብርናው መሣሪያዎችም እምነት ጾም ጸሎት ፍቅርና ልዩ ልዩ ትሩፋትን ያመለክታሉ ። ዘሩ ቃለ እግዚአብሔር (ወንጌል) ነው ፤ እርሻው ልበ ምእመናን ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወርኃ ዘርእ በገሊላ ባሕር ዳር ያስተምር ነበር ። በትምህርቱና በተአምራቱ ተማርከው ሊሰሙት ወደ እርሱ የመጡት ሰዎች እጅግ ብዙ ነበሩ ። ከዚህ በኋላ ወደ መርከብ ገብቶ ሲያመትር የአካባቢውንም ገበሬዎች ሥራቸውን እየተዉ ትምህርቱን ለመስማት ወደ እርሱ መጡ ። እነሱንም ባየ ጊዜ በምሳሌ ሊያስተምራቸው ፈለገ ትምህርቱንም ሲጀምር "ናሁ ወጽአ ዘራኢ ይዝራእ" እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ በሚል ነበር ።

በዚሁ ምሳሌያዊ ትምህርቱም የዘሩን አወዳደቅ ሲተነትን ዘሩ በመንገድ ዳር ፤ በጭንጫ ፤ በእሾህ መካከል በመልካም መሬት ላይ መውደቁን ገልጾ በመንገድ ዳር የወደቀው ቢበቅልም በእግረኞች ተረግጦ እንደጠፋ ፤ በጭንጫ ላይ የወደቀውም ፈጥኖ ከበቀለ በኋላ ሥር የሚሰድበት አፈር ስላልነበረው ደርቆ እንደጠፋ ፤ በእሾህ መካከል የወደቀውም በቅሎ አደገ ነገር ግን እሾህ አንቀው ፍሬ እንዳይሰጥም ከለከለው አለ ፤ የዚሁ ምሳሌያዊ ትምህርት ከዚህ በላይ የተገለጸው ሰሙ ሲሆን ወርቁም ዘሩ ቃለ እግዚአብሔር ነው መንገድ ዳር ጭንጫ እሾህ የተባሉ ቦታዎች በልዩ ልዩ ሀሳብ ክፋትና ተንኮል የተሞሉ የሰዎች ልብ ነው ።

በመልካም መሬት የወደቀው ዘር ግን አንዱ ሠላሳ ፤ አንዱ ስልሳ ሌላው መቶ ፍሬ ሰጠ ይላል ። የዚህ ምሳሌ በጭምቶች ፤ በአስተዋዮችና በብሩኅን አእምሮ ምእመናን ልብ ያረፈው ቃለ እግዚአብሔር የተቀደሰ (ምግባር ትሩፋቱን) ለእግዚአብሔር እንደቀረቡ ያመለክታል ፤ ምተርጉማን ሊቃውንትም ስለሦስቱ የፍሬ አሰጣጥ ደረጃ ሲሰጡ የወጣንያን ፤ የማዕከላውያን ፤ የፍፁማን ምሳሌ ነው ይላሉ ። በእርግጥም ነው ።

ስለሆነም ወርኃ ክረምት በተለያየ መንገድ ስንመለከተው የተለያዩ ትምህርቶች ይሰጠናል ። ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዘርና ስለወርኃ ክረምት ጠቃሚነትና ጎጅነት በምሳሌ ያስተማረንን ከቅዱስ ወንጌሉ በሰፊው እንገነዛባለን በሁለተኛ ደረጃም ራሱ ወርኃ ክረምቱ ምን እንደሚያስገኝና ምንን እንደሚያስከትል በዓይናችን በምናየው በጆሮአችን በምንሰማው በሰፊው እንረዳለን ።

የዝናም ጥቅም አዝርዕትን ፤ አትክልትን ፤ ዕፀዋትን ሣርንና ሌላውንም አብቅሎ በፀሐይ አሳድጎ አብስሎ ፍጥረቱን ሁሉ ይመግባል ጉዳቱ ደግሞ ወጨፎው ጎርፉ ፤ ዶፉ ፤ በረዶው ብዙ ንብረትና ሀብት ሰውና ከብት ጠራርጎ ይወስዳል ያጠፋል ።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላክ እያንዳንዳችን ልባችን በመንገድ ዳር ፤ በጭንጫና በእሾህ መካከል እንደ ወደቀው ዘር ፍሬ ሳይሰጥ እንደቀረው ሳይሆን በመልካም መሬት እንደበቀለውና ሠላሳ ስልሳ መቶ ፍሬ እንደሰጠው ዘር በእምነታችን በትሩፋቶቻችን በፈጣሪያችን ፊት የተመሰገንን ሆነን ለመገኘት እንድንችል ሰሚ ጆሮ አስተዋይ አእምሮ ይስጠን ፤ ወርኃ ክረምቱንም የበረከት፤ የጤናና የፍቅር የአንድነትና የሰላም ወቅት ያደርግልን ዘንድ የተቀደሰ ፈቃዱ ይሁንልን ።

ሊ/ት ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም

# አምልኮት

ሰማይና ምድርን የፈጠረ ፣ በውስጣቸው ያሉትንም ግዙፋንና ረቂቃን ፍጥረታት ሁሉ ያስገኘ እግዚአብሔር አምላክ መመለክ የባሕርዩ ነው ። ለማንኛውም ነገር ሠራዒና መጋቢ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ከማይመረመረው ገናና ክብሩ የተነሣ በሰው ልጅ እንደበት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ግዑዛን ፍጥረታት ይመሰገናል ይመለካልም ።

ስለዚህም ነው ነቢዩ ዳዊት "...ፀሐይና ጨረቃ ያመሰግኑታል ከዋክብትና ብርሃን ያመሰግኑታል ። ሰማየ ሰማያት ያመሰግኑታል..." ሲል የተነገረው መዝ ፻፵፰ ቁ ፫ ሁኖም ከረጅም ዓመታት በፊት የነበሩ አንዳንድ ሰዎች የልዑል እግዚአብሔርን ታላቅነት ካለመረዳት የተነሣ በተለያዩ ሰው ሠራሽ ነገሮች ያመልኩ ነበር ። በዚህም በተሣሳተ ሕይወት ይጓዙ የነበሩ ሰዎች በነቢያት ተወቅሰዋል አድራጎታቸውም ከንቱ እንደሆነ ተገልጿል ፩ኛ ነገ. ፲፰ ፳፮—፳፱ ይህንም አስከፊ ስሕተት በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ በተደጋጋሚ ይገለጽ ነበር መሳ ፪ ፲፩—፲፭ ።

በዐያሌ ቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ እንደሚገኘው ትዕዛዛትን ካለመጠበቅ የተነሣ ከሚፈጸሙት ስህተቶች መካከል በጣኦታትና በሌላም ሰው ሠራሽ ነገር ማምለክ ልዑል እግዚአብሔርን በማስቆጣት ከፍተኛውን ሥፍራ ይይዛል ይህም "...ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ የማናቸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸውም አታምልካቸውም በሚጠሉኝ እስከ ሦሥትና አራት ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች የማመጣ ለሚወዱኝና ትዕዛዜን ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምህረትን የማድረግ ቀናተኛ አምላክ እኔ ነኝ..." ዘጸ ፳.፭—፮ ሲል እግዚአብሔር አምላክ የሰጠውን አምላካዊ ትዕዛዝ መገንዘብ ለማንኛውም የሰው ዘር አስፈላጊ ነው ። በዚህም ትዕዛዝ መሠረት የሚመለከው እግዚአብሔር የሚመሰገነውና የሚሰገድለትም እርሱ ብቻ ነው መመለክ መመስገንና ስግደት የባሕርይ ገንዘቡ ነውና ።

እግዚአብሔር ወልድ ከቅ/ድንግል ማርያም ተወለደ ሰው ሁኖ በዓለም በተገለጸ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት የሰዎች መዳን የምሥራች የሆነችውን ወንጌል አስተማረ ሐዋርያትም ወንጌልን ተምረው ከጌታ ተልከው በዓለም ወንጌልን ሲሰብኩ ሊመለክና ሊሰገድለት የሚገባ ምስጋናም የባሕርዩ የሆነ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ገለጸ ። በዚህም የሐዋርያት ወንጌላዊ ትምህርት የጣኦታት ቤተ መቅደሶች ፈራረሱ አብያተ ክርስቲያናት ታነጹ ።

ቅዱሳን ሐዋርያትም በትምህርታቸው ከአምልኮ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር የመለሱአቸውን ምዕመናን ወደ ጣኦት ቤተ መቅደስ እንዳይሄዱ ከዝሙት እንዲርቁ ለጣኦት የተሰዋውን እንዳይበሉ አስተምረዋል ። ይህንም በቅዱስ ሲኖዶሳቸው ወስነው ለክርስቲያኖች ሁሉ አስተላልፈዋል የሐዋ ሥራ ፲፭. ቁ. ፲፱—፳፯ ።

ይሁን እንጂ ቀደም ሲል በሐዋርያት የተወገዘውን ወደ ጎን በመተውና በመዘንጋት ወደ ጣኦት ቤት በመሄድና ለጣኦትም በመሰዋት ላይ የሚገኙ አሁንም አሉ በተለይም በግንቦት ወር አካባቢ በአገራችን በአንዳንድ አካባቢዎች ንፍሮ እያነፈሩ ዳቦ እየጋገሩ ቆሌየ ጠባቂየ ...እያሉ የተለያዩ የርኩሳን መናፍስት ስሞችን በመጥራት የዛሬ ዓመት አድርሰን እያሉ ንፍሮውን ቆሎውን ዳቦውን በየመንገዱ የሚበትኑ አልጠፉም ።

ይህ መጥፎ አድራጎታቸው ኢኮኖሚን ከማዳከም በስተቀር ምንም ዐይነት ጥቅም እንደሌለው ሲነገራቸው እንቆስላለን እንደማለን ከዓመት ወደ ዓመት አንሸጋገርም በማለት እውነት አልባ የሆነ ሰይጣናዊ ስህተት ይፈጽማሉ ።

በመሠረቱ ከዓመት ወደ ዓመት የሚአደርስ (የሚአሸጋግር) የረጅም ዕድሜም ዕድለኛ የሚአደርግ መመለክ የባሕርዩ የሆነ እግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው ኢሳ.፵፯ ፱—፲፪

በተለይ በአንዳንድ ጠረፍ አካባቢ የሚኖሩ ወገኖች እስከአሁን ድረስ የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ ያልደረሳቸው በመሆኑ በጫካ ያሉትን ዛፎችና ተራራዎች ገና በማምለክ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ሰዎች ገና የዘመናዊ አስተሳሰብ ሕይወት አልገባቸውም የሥልጣኔውም ጮራ እምብዛም አልፈነጠቀባቸውም።

እንግዲህ በአጠቃላይ ጣኦት ማምለክ ሲባል እንደቀድሞ ዘመን ሰዎች ለልዩ ልዩ ምስሎች መስገድ ብቻ ይሆን በሀብት በጉልበት በዘመድ በአዝማድ በሌላም ነገር መመካት ከጣኦት ማምለክ አንዱ ሥነ ባሕርይ ነው "...ኃይለኛ በኃይሉ አይመካ ጥበበኛም በጥበቡ አይመካ የሚመካስ እግዚአብሔርን በማወቅና ሕጉ



www.ethiopianorthodox.org

ንና ትዕዛዙን ልብ በማድረግ ይመከ..." ተብሎ ተጽፎአልና ።

በሌላ በኩል ደግሞ "እንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚአመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮት ከንቱ ነው ። ንፁሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ ግን በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለም ከሚገኝ ዕድፍም ሰውነትን መጠበቅ ነው..." ያዕ ፩ ፳፮—፳፯ በማለት ሐዋርያው ቅ. ያዕቆብ የጻፈውን መመልከት ስለ አምልኮተ እግዚአብሔር ያለውን ግንዛቤ ግልፅ ያደርገዋል። ስለዚህ እግዚአብሔርን የማምለክ ትርጉሙ እስከፊ ነገሮችን ሁሉ ለመጨረሻ ጊዜ ከሕሊና አስወግዶ በመልካም ሥነ ምግባር ለሕገ እግዚአብሔር መታዘዝና አቅመ ደካሞችን መርዳት ነው ።

መ/ ኤፍሬም በየነ

# ትምህርት ለሁሉ ይዳረስ

የትምህርት ዓይነቱ ብዙ ቢሆንም እንደብዛቱ ጥቅሙም ያንኑ ያህል ነው ቁም ነገሩ ግን ተምሮ መገኘትና የተማሩትን ትምህርት ለሌላ ከማስተላለፉ ላይ ነው ። ቀደም ብላ የትምህርትን ጠቃሚነት የተረዳችውና በሐዋርያት ጉባኤ የተሰበሰበችው አንዲቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከተጣለባት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት አኳያ የወንጌልን ትምህርት ለማዳረስ አመርቂ የሆኑ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ትገኛለች ።

ይሁን እንጂ ትምህርት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ብዙ ጥፋቶች ሲከሰቱ ይታያሉ ይኸውም ድንቁርና በሰው ላይ ሲገለጽ እንደ ጨለማ ሆኖ ሲጋረድ ፡ ስርቆት ፡ በሐሰት መመስከር ፡ አድልዎ የፍርድ እርስበርስ አለመግባባትና አለመተዛዘን መፋታት ግድያና ዝርፊያ ራስን መውደድ እኒህንና እነዚህን የመሳሰሉ ሁሉ በሀገር ላይ የሚታዩት ወንጌል ባልተሰበከባቸውና ትምህር ባልተማሩ ሰዎች ዘንድ መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም ። እኒህን ለማስወገድ የወንጌል ትምህርት አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ከዚህም የተነሣ ልዩ ልዩ ታሪኮች በዘገባቸው አያሌ ድርሳናት በሰው ልጆች መካከል ያለውን የኑሮ ምስቅልቅልና አለመግባባት በቶሎ መፍትሔ የማይገኝላቸው አስፈላጊ ነገሮችም እንዳሉ በሰፊው አትተዋል ። ስለዚህም ሚስተር ምንጅ የተባሉት ስዊድናዊ ሊቅ "ህይወት ለፍጡራን" በተሰኘው ድርሰታቸው አስተያየት ሲሰጡ የሰውን ልጆች የኑሮ ውጣ ውረድና የሕይወታቸውን ኑሮ ስንመለከተው መጨበጫና መያዣ የሌለው መሐንዲስ አንድ ጊዜ እንደቀየሰው ሆኖ የማይገኝ ነፋስና ወጀብ ሳይነካው ፈርሶ የሚያድር አሳዛኝ ህንፃ ነው" ብለውታል ።

እንደኚህ ምሁር አባባል በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረው የሰው ልጅ የተሰጠውን የህግ ሰንሰለት ነው ከማጥበቅ ይልቅ እየላላ አውልቆ በመጣል ከትህትና ይልቅ ትእቢትን ከእሽታ ይልቅ እምቢታን የሚያስቀድም ኃይለኛ ተሚጋች ሆኖ እራሱን በራሱ እየሞገተ ተረቶ ሲወድቅ ይታያል ። ይህም ሊሆን የሚችለው ሀሳብ ለሀሳብ ተግባብቶ ተባብሮ በመሥራትና ባንድ ዓላማ ቆሞ አካባቢውንና ጠባዩን ለራሱ በሚያመቸው አኳኋን ለውጦ ጥቅም ላይ በማዋል ፈንታ ክርክርንና ጭቅጭቅን ተንኮልንና ምቀኝነትን ሀሜትንና አሉባልታን በመፍጠር እራሱን በድሎ ከሰው ጋር ብቻ ሳይሆን ከፈጣሪው ጋር ይጣላል ይኸውም ትምህርት ካለመዳረሱ መሆኑን ለመረዳት አያዳግተንም ።

ለሁሉም ትምህርት ከተዳረሰ ግን የድንቁርና መጋረጃ ተገፎ ወድቆ ጨለማውም በእውቀት ብርሃን ሊለወጥ የሚችለው ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መምህራንን በብዛት አሠራጭታ ህዝቡ ትምህርት ሲደርሰውና ሰበካ ጉባኤም ተጠናክሮ የሰበካ ጉባኤን ግንባታ በተፈለገው ፍጥነት ለማራመድ ሲቻል ነው ። ይህ ሲሆን ለሰበካ ጉባኤ መጠናከር ለቤተ ክርስቲያን እድገት ለወንጌል መስፋፋት ለምእመናን ብዛት ታላቅ አስተዋጽኦ ማበርከት ብቻ ሳይሆን ሰዎች ኑሮአቸውንና ህይወታቸውን እያጠፈጡ ከከፉ ሥራቸው እየተመለሱ በሀገርና በወገን በቤተ ክርስቲያን ፍቅር እንደሚጠመዱ የታመነ ነው ።

ይህ ከሆነ የመተዛዘንና የመተሳሰብ ኑሮ እንዲስፋፋና ፍቅርም ሥር እየሰደደ እንዲሄድ በሁሉም ዘንድ ድጋፍ ያገኛል በመሆኑም የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የሀገር እድገት የሚፋጠነውም ሆነ ባለበት ሊሄድ የሚችለው አለበለዚያም ወደኋላ የሚቀረው በብዙ ምክንያቶች ቢሆንም እያንዳንዱ ዜጋ በቅንነት ኃላፊነትን በመረዳት መብትና ግዴታውን በትክክል ሲገነዘብና ለዚህም አስፈላጊው ትምህርት ሲደርሰው እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም ይህን ለማወቅ ከተፈለገ ተምረው የሰለጠኑ ሕዝቦች የስልጣኔን ጎዳና ተከትለው የእድገት መመሪያቸውንም በዚህ አቅጣጫ ቀይሰው ከሠሩት የሥራ ፍሬ የተገኘውን በረከት ከነውጤቱ መረዳት ታላቅ ምስክር ነው።

ይኸውም አብዛኛው ሕዝብ ትምህርት የተዳረሰው በመሆኑ መቼ? ለማን? ለምን? እንደሚሠራ ጠንቅቆ ያውቃል እንጂ እርስ በርሱ እየተለያየ በሆነ ባልሆነው ሲጣላ አይታይም። ይህም ደግሞ የአመለካከት ብስለቱንና የትምህርቱን የእውቀቱን የሥልጣኔውን ደረጃ ከቀን ወደ ቀን እያደገ መሄዱን የሚያመለክት ስለሆነ አርአያነቱ የጎላ ነው።

በቤተ ክርስቲያናችንም በኩል ቢሆን አሮጌውን አስተሳሰብ ትቶ የተሻለውንና አዲስ ሥራዎችንና ሥርዓቶችን በመተካት የአመለካከት ለውጥም እንዲያሳይ በሰበካ ጉባኤ በኩል የተቋቋመው ቃለ ዓዋዲ ከመረጥነው የእድገት አቅጣጫ ጋር እንዲጣጣም አያሌ ጥረቶች ተደርገዋል ለውጡ የሥራ ለውጥ እንጂ የእምነት ለውጥ አያደርግም ።

ሃይማኖት ፀንቶ ከመኖር በቀር እንደሌላ ነገር አይለወጥም ሃይማኖት ጊዜን ይለውጣል እንጂ ጊዜ ሃይማኖትን አይለውጥምና ነው ። የሥራና የሥነ ሥርዓት ለውጥ ግን ያስፈልጋል ። ይህም ከተግባር ላይ ሊውል የሚችለው የወንጌል ትምህርት ለሁሉ ሲዳረስ ነው ትምህርት ያልደረሰው ሕዝብ ግን ስለሥራና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ተለወጠ ብለው ቢነግሩት እምነት የተለወጠ እየመሰለው ግራ ይገባዋል ።

ለምሳሌ አዲስ ዘመን መጋቢት ፱ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም (ደርስዳይጀስት) ከተባለው መጽሔት ወስዶ በምሳሌ ያቀረበውን እንመልከት፡

"ሊንዳ የተባለች አሜሪካዊት ሴት ባለቤቷ ካለበት መሥሪያ ቤት ተለውጦ ወደሌላ አገር ተዛውሮ እርሷ ግን የሥራውን ለውጥ በመጥላት ከባሏ ጋር አልሄድም አለች" ይላል አንዳንድ ቀሳውስት በሰበካ ጉባኤ የተገኘውን ለውጥ ማለት ከትምህርት ማነስና ከራስ ወዳድነት የተነሣ የንስሐ ልጆቻቸውን የሰበካ ጉባኤ አባል ሆነው የገንዘብ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ትምህርት መስጠትና ተመዝግበውም አባል እንዲሆኑ አይፈልጉም ። ለምዕመናን በየቀኑ ከ፲፡፴—፲፱ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ባለው የወንጌል ትምህርት በሚሰጥበት አዳራሽ እነስ ያሉት ሲገኙ በርከት ያሉት ካህናት የትምህርቱ ተካፋይ በመሆንና ምእመናኑም ተካፋይ እንዲሆኑ የመገፋፋት ፍላጎት አይታይባቸውም ።

በተጨማሪም ባለፈው ጊዜ የነበሩት የቤ/ያን ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው በኢትዮጵያ ሰሜን ወደሚገኙት የዜማ ፡ የቅኔ፡ የመጽሐፍ ትርጓሜ ትምህርት ቤት እየገቡ እያጠኑ ለምነው እየበሉ ትምህርትን ከቀሰሙ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግሉ ነበር። አሁን በአ.አ አድባራትና ገዳማት የሚገኙት ካህናት ግን ከጥቂቶቹ በቀር አብዛኞዎች በየወሩ ደመወዝ እየተከፈላቸው የቅኔ መምህር የዜማ የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር ተቀጥሮላቸው መማር ደስ አይላቸውም ።

መምህራኑም የሚያስተምሩት አጥተው ቁጭ ብለው ይውላሉ እንዲህ ያለውም ሁኔታ ቤ/ያናችን ያመጣችውን የተሐድሶ ለውጥ አለመቀበል ነው ለውጥን እንደ አመጣጡ መቀበል እንጂ ለውጥን መቃወም እድገትንና ሥልጣኔን የሥራ ተሀድሶንም ወደኋላ የሚያስቀር የደካማነት ጠባይ ነው ።

ይህን መሳይ ተቃውሞ ያረጀና ያፈጀውን የኑሮ አስተሳሰብ ጠባይ የሆነውን ግለኝነትን ስግብግብነትን ራስ ወዳድነትን ሁሉ ለኔ ፡ ለእኔ ብቻ ማለትን የሚያስከትል ሆኖ እናገኘዋለን ይህም የሚያሳየን ሰው ትክክለኛውን ትምህርት ያገኘ እንደሆነ ለስላሳና ገር እግዚአብሔርን የሚከተል ፍጥረት ነው ። ትምህርት ያላገኘ እንደሆነ ግን በምድር ላይ ካሉት አራዊት ሁሉ የባሰነው እንደሚባለው እንዳይሆን ቅ/ቤ ያናችን ሁሉ እንዲማር የወንጌል ትምህርት ለሁሉ እንዲዳረስ ማድረግ ይፈለግባታል ዓላማውም ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ጤናችን

የሰው ልጅ ከሁሉ በፊት ሊያስብበትና ሊጠበብለት የሚገባው ስለጤንነቱ ይዘት መሆን እንደሚገባው ማይንስም ቅዱሳት መጻሕፍትም ያረጋግጣሉ ።

ስለሆነም ሰው በጤና ለመኖር ስለጤና የተጻፉ ሕጎችን ማክበር የሚጠቅመው ይሆናል ።

ስለጤና መሠረታዊ አመጣጦች በዚህ ዓምድ እንደምናቀርብ በተደጋጋሚ ገልጸናል ። ወቅቱም ስለጤናችን የምንወያየበትና ለቀሳፊ በሽታዎች መከላከያ ዘዴዎችን የምንፈልግበት በመሆኑ ስለ





www.ethiopianorthodox.org

ጤንነታችን ልንማር ይገባል ።

እንግዲህ "ተላላፊ በሽታና ክትባት "ከተሰኘው አጭር መጽሐት ዶ.ጋግመን ለመግለጽ እንደ ሞከርነው፡ በሣሬው ዝግጅትም የሚከተለውን እናቀርባለን ።

## የኩፍኝ ክትባት

ኩፍኝን ለመከላከል የሚቻለው ሕፃናትን በማስከተብ ብቻ ነው ። ይህንንም መመሪያ አክብረው የሚጠቀሙ ወላጆች ልጆቻቸውን ከክፍኝና ከመሳሰሉት ሊያጽናቸው ችለዋል ።

በክትባት ብቻ መከላከያ መድኃኒት የሚያገኙ ልዩ ልዩ የበሽታ ዓይነቶች አሉ ። ከነዚህም ይኸው የኩፍኝ በሽታ አንዱ ነው ።

የጤና ሊቃውንት እንደሚያስተምሩት አንድ ሕፃን ተወልዶ ስድስት ወር እስከሚሆነው ድረስ ለኩፍኝ በሽታ ከእናቱ የወረሰው የመከላከያ ኃይል ይኖረዋል ይላሉ ።

ከነዚህ የስድስት ወራት ጊዜ በኋላ ግን የመከላከያው ኃይል እየደከመ ስለሚሔድ በሽታው በቀላሉ ሊይዘው ስለሚችል ዘጠኝ ወር ሲሆነው የኩፍኝ ክትባት እንዲከተብ ማድረግ የወላጆች ግዴታ ነው በማለትም ያስተምራሉ ።

ወላጆች በዚህ መሠረት ዓላማ ፀንተው ሕፃኑ ክትባቱን ከተከተበ ለብዙ ዓመታት በበሽታው ሊጠበቅ ስለሚችል እንደሌሎች ክትባቶች መደጋገም አያስፈልግም ።

የኩፍኝ ባሽታ ዕድሚአቸው ከአንድ ዓመት በታች በሆኑ ሕፃናት ላይ የሞት አደጋን ሊያደርስባቸው ስለሚችል ክትባቱ ከላይ በተጠቀሱት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲወስዱና ከመከተባቸውም በፊት ኩፍኝ ከያዛቸው ልጆች ጋር እንዳይገናኙ መከላከል እጅግ አስፈላጊ ነው ።

የኩፍኝ ወረርሽን በሰፈሩ ከገባ በኋላ ክትባቱ ቢሰጥ በሽታው በሕፃኑ ላይ እንዳይበረታበትና ወደ ሌላም ቦታ እንዳይዛመት ከመርዳቱም በቀር ሕፃኑን ከበሽታው ለመጠበቅ ዋስትና የለውም፡ ስለዚህ ሕፃኑን በተጠቀሰው ጊዜ አስቦ ማስከተብ ሕፃኑን ከሕመም ወላጆችም ከጭንቀትና ከኢኮኖሚ ቀውስ ሊያድን ይችላል ።

ወደ ቤተ ክርስቲያናችን መለስ ስናደርገውም ቃሉን ሰምተው በቃሉ መሠረት የሚኀዙ ሁሉ ከልዩ ልዩ ፈተና እንደሚጠብቁ እንማራለን "ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የመሠረተ ሰውን ይመስላል" ይላልና ማቴ·7 ቁ·24 ።

እንግዲህ የተጻፈው ሁሉ ለእኛ መማሪያ መመከሪያ ነው ፡ ቤተ ክርስትያን ለሰው ልጅ መንፈሳዊና ሥጋዊ ድኅንነት የሚገኝባቸው መመሪያዎች አሉአት እኒህንም አክብሮ የሚጠቀምባቸው ቤቱን በማይነቃነቅ መሠረት ላይ እንደመሠረተ ሰው ይቆጠራል ፡ ምክንያቱም ከማንኛውም ችግር ተጠብቆ እንዲኖር ያስችለዋልና በማይንስም የተጻፈው ይህንኑ የሚመስል በመሆኑ ትእዛዙን አክብሮ የሚፈጽም ሁሉ ብልህ ነው ። ጤናውን ከመጠበቁና የቤተሰቡን ጤና ከማስጠበቁም ሌላ ከገንዘብ ወጭና ከአእምሮ ጭንቀት ሊድን ይቻላል ።

ስለዚህ ልጅዎን በማስከተብ ጤናውን ያስጠብቁ እርስዎም በጤና ምክንያት ለሚያጋጥምዎ ችግር ይላቀቁ እንላለን ።

ሊቀ\ካህናት በለጠ አበበ

# ጋብቻና

# ኀብረተ ሰብእ

በዓለማችን ውስጥ የሚመሠረተውን ኅብረተሰብእ አጤነን ስን መለከት ሁለት አቅጣጫን ይዞ እናገኘዋለን አንዱና ዋነኛው ክፍል የሆነው የኅብረተሰብእ መገኛ ጋብቻ ነው ።

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የማይደገፈውና ኅብረተሰቡእን ወደ መጥፎ አዝማሚያ የሚመራው ከጋብቻ ውጭ በሚፈጸመው ግንኙነት የሚገኘው አሳዛኝ ኅብረተ ሰብእ ነው ።

የእነዚህን ሁለት ክፍሎች ታሪካዊ ይዞት በአጭር እናቀርባለን ። የጥንቱ ወግ ሆኖ የቆየውና በኋለኛው ዓለም እየተወገዘና እየተጠላ የሔደውን የጋብቻ ዓይነት ያስፈጽሙ የነበሩት ወላጆች ነበሩ ተጋቢዎቹ ሳይተዋወቁ እንዲያውም አልፎ ተርፎ መልክ ለመልክ እንኳን ምን እንደሚመስሉ ሳይተያዩ በወላጆች ተፅዕኖ ታፍነው በጫጉላ ቤት ብቻ የሚተዋወቁ ባልና ሚስቶች እንደነበሩ የትናንቱ የሀገራችን ባሕላዊ ትዝታ ሲሆን ዛሬም በአንዳንድ የገጠሩ ኢትዮጵያ ሲፈጸም እንመለከታለን ።

ይህን የመሰለ ጋብቻ ይፈጸሙ በነበሩት ወገኖች በተለይ ሴቲቱ አካለ መጠን ሳታደርስ ከ፱ ዓመት እስከ ፲፩ ዓመት በአለው ጊዜ ጋብቻ ለመፈጸም ስለምትገደድ ለዚህ ጉዳይ አካሏ የማይመጥን የተፈጥሮ ሕይወቷ ለጋብቻ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ባሏን ትጠላለች ፡ ስታየው ኀዳ ትገባለች ስትመለከተው ዝግንን እያላት ሥቃይ ስለሚሰማትና የሥቃይዋ መነሻ ርሱ

(ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል)



ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቱና እየተረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ·
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org